ashamlaws.wordpress.com


# የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት
# ደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ
# DEBUB NEGARIT GAZETA
# OF THE SOUTHERN NATIONS, NATIONALITEIS AND PEOPLES' REGIONAL STATE

ዓመት ቁጥር 161/2008
ሀዋሳ____ ቀን 2፻፰ ዓ.ም

በደቡብ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ አዋጅ

Year No 161 Hawassa
________/2015


**አዋጅ ቁጥር ፻፷፩\፪፻፰**

**የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ፣**

**መግቢያ**

የክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር የልማትና የመልካም አስተዳደር ሥራዎቻችን ከደረስበት ዕድገት ደረጃ አንጻር ፈትሾ ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የክልላችንን የኢኮኖሚ ዕድገት በላቀ ደረጃ ለማፋጠን የአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት የተልዕኳቸውን ስፋትና ተቀራራቢነት መሰረት ያደረግ መሆን እንዳለበት በመታመኑ፣

በተሻሻለው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ-መንግስት አንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 3 (ሀ) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

**Proclamation No 161/2015**

**A proclamation To Provide for Redefinition of the Powers and Duteis of Executive Organs of Southern Nations, Nationalities and Peoples' Regional State,**

## Preamble

**Where as,** it has been found vital to correct the power and duty, and organization of Executive ogans of the regional government from the point of view of development and good governace activities growth stage has reached;

**Where as,** it has been believed that organization of executive organs shall be on the basis of the wideness and propinquity of their missions in order to fasten the economic growth more better in the region;

**Now, therefore,** in accordance with article 51 sub-article 3/a/ of the revised constitution of the Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State hereby proclaimed as follows;

ashamlaws.wordpress.com

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፻፷፩/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፦

1) **"ክልል"** ማለት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ነው፡፡

2) **"ክልል ምክር ቤት"** ማለት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ምክር ቤት ነው፡፡

3) **"መስተዳድር ምክር ቤት"** ማለት በተሻሻለው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 65 መሠረት የተገለጸው ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ከፍተኛ የአስፈፃሚ አካል ወይም ካቢኔ ነው፡፡

4) **"አስተዳደር ምክር ቤት"** ማለት እንደ አግባብነቱ የዞን፣ የከተማ አስተዳደር፣ የልዩ ወረዳ፣ የወረዳ አስተዳደር አስፈፃሚ አካል ወይም ካቢኔ ነው፡፡

5) **"አስተዳድር እርከን"** ማለት እንደ አግባብነቱ በክልሉ የሚገኙ የዞን፣ የልዩ ወረዳ፣ የወረዳ፣ የከተማ፣ የክፍለ ከተማ እና የገጠርና ከተማ ቀበሌ አስተዳደርን ያጠቃልላል፡፡

## PART ONE
## GENERAL

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as" The Redefinition of the Powers and Duties of Executive Organs of Sothern Nations, Nationalities and Peoples' Regional State Proclamation No 161/2015"

**2. Definition**

In this proclamation unless the context otherwise requires;

1. **"Regions"** shall mean southern Nations, Nationalities and Peoples' State;
2. **"Regional Council"** shall mean Southern Nations, Nationalities and Peoples' Regional Government Council;
3. **"Administrative Council"** shall mean Higher executive body or Cabine which prescribed in sub-article /1/ of article 4 in this proclamation where it is stated based on the amended Southern Nations, Nationalities and Peoples' Constitution article /65/;
4. **"Administration Council"** shall mean executive body or cabine, as it is relevance, of Zone, special woreda, Hawassa city administration, woreda administration;
5. **"Administration Hierarchy"** shall mean include the Zone, special woreda, woreda, city, sub-sity, kebele administration Rural and City ;

6.**"የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤት"** ማለት ቢሮ፣ ኮሚሽን፣ ኤጀንሲ፣ ኢንስቲትዩት፣ ጽሕፈት ቤት፣ ባለስልጣን መሥሪያ ቤት እና ሌሎች የመንግሥት አስተዳደር ተግባር ለማከናወን በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጐች መሰረት የተቋቋሙትንና በሥራቸው ያሉትን መሥሪያ ቤቶችን ያጠቃልላል፡፡

7. **"ቢሮ"** ማለት ለመስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪ የሆኑ የክልሉ አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ናቸው፡፡

8. **"ኃላፊ ወይም ምክትል ኃላፊ"** ማለት እንደቅደም ተከተሉ የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶችን በበላይነት ለመምራት በኃላፊነት የተሾመ ወይም የተመደበ ኃላፊ ወይም ምክትል ኃላፊ ነው፡፡

9. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለአስፈፃሚ አካላት መስሪያ ቤቶች

### 3. መቋቋም

1) የሚከተሉት የአስፈፃሚ አካላት መስሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡፡

1) የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
2) የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ
3) የእንስሳትና የዓሣ ሀብት ቢሮ
4) የአርብቶ አደር ጉዳይ ቢሮ

6. **"Office of Executive Body"** shall mean Bureaus, commissions, Agencies, Institutes, Offices, Authorities and other offices established based on this proclamation and other laws to perform state administration function including offices under them;

7. **"Bureau"** shall mean executive organizations of the region which are accountable to administrative council,

8. **"Head or Deputy Head"** shall mean head or deputy head nominated to head executive organ offices consecutively;

9. **"Person"** shall mean natural person or an organ owned personality by law.

## Part Two
## Executive Organ Offices

### 3. Establishment

1. Where the following executive organ offices are established in accordance with this proclamation;

1. Finance and Economy Development Bureau;
2. Agricultural and Natural Resource Development Bureau;
3. Animals and Fish Resource Bureau;
4. Pastorial Affair Bureau;

5) የውሃና የመስኖ ልማት ቢሮ
6) የንግድና የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ
7) የከተማ ልማት እና ቤቶች ቢሮ
8) የኮንስትራክሽን ቢሮ
9) ትራንስፖርትና የመንገድ ልማት ቢሮ
10) የገቢዎች ባለሥልጣን
11) የትምህርት ቢሮ
12) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ
13) የጤና ቢሮ
14) የሴቶች እና ሕፃናት ጉዳይ ቢሮ
15) የወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ
16) የባህልና ቱሪዝም ቢሮ
17) ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማትና ቢሮ
18) የፍትህ ቢሮ
19) የፀጥታና አስተዳደር ቢሮ
20) የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት
21) የአካባቢ ጥበቃና የደን ባለሥልጣን

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተራ ቁጥር 1 እስከ 20 የተመለከቱት የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች ተጠሪነት ለክልሉ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤትና ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል፡፡

3) የአካባቢ ጥበቃና ደን ባለሥልጣን ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል፡፡

5. Water and Irrigation Development Dureau;
6. Trade and Industry Development Bureau;
7. Urban Development and Houses Bureau;
8. Construction Bureau;
9. Transport and Road Development Bureau;
10. Revenue Authority;
11. Educational Bureau;
12. Technical and Vocational Education and Training Bureau;
13. Health Bureau;
14. Women and Children Affair Bureau;
15. Youths and Sport Bureau;
16. Cultural and Tourism Bureau;
17. Public Service and Human Resource Development Bureau;
18. Justice Bureau;
19. Security and Administration Bureau;
20. Public communication Affairs office;
21. Environmental and Forest conservation Authority.

2. Executive organ organizations jot-down from 1 upto 20 which established based sub-article 1 of this article, shall be accountable to the president and regional government administrative council;
3. Environmental protection and Forest shall be accountable to the president.

4. ስለሌሎች የአስፈጻሚ አካላት መስሪያ ቤቶች

1) በዚህ አዋጅ ውስጥ ያልተመለከቱ ሌሎች የክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ አካላት በማቋቋሚያ ሕጎቻቸው መሰረት ስራቸውን ይቀጥላሉ።

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሥራ ላይ ያሉና ወደፊት የሚቋቋሙ አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት በሚመለከት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ መሠረት ይወሰናል።

## ክፍል ሦስት

## ስለርዕሰ መስተዳድሩ፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር እና መስተዳድር ምክር ቤት

5. መስተዳድር ምክር ቤት

1) የሚከተሉት የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት ናቸው፣

ሀ) ርዕሰ መስተዳድሩ፣

ለ) ምክትል ርዕሰ መስተዳድር፣

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 ከተራ ቁጥር ከ1 እስከ 20 የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላትን የሚመሩ ኃላፊዎች፣እና

መ) በርዕሰ መስተዳደሩ የሚሠየሙ ሌሎች ኃላፊዎች።

**4. Other Executive Organ Offices**

1. Other regional government executive organs which are uncovered by this proclamation shall carry on their functions by their establishment laws;
2. Without prejudice the provision in sub-article /1/ of this article, concerning the structure of executive organs shall be determined by the regulation to be issued by administrative council;

## Part three

## Chief Executive, Vice-Ehief Executive and Administrative Council

**5. Administrative Council**

1. Administrative council shall have the following members:-

   a) Chief executive;

   b) Deputy chief executive;

   c) Heads heading the executive bodies specified from 1 upto20 under sub-article /1/ article /3/ of the proclamation: and;

   d) Other officials to be designated by the chief executive

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) የተመለከተው ማንኛውም ኃላፊ በመስተዳድር ምክር ቤቱ ስብሰባ የመገኘት ግዴታ አለበት፡፡ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መገኘት በማይችልበት ጊዜ ምክትሉ ወይም ካንድ በላይ ምክትሎች ባሉ ጊዜ፤ በግልፅ ተለይቶ በፅሁፍ ውክልና የተሠጠው ምክትል ኃላፊ ወይም በግልፅ ተለይቶ በፅሁፍ ውክልና የተሠጠው ከሌለ በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ኃላፊ በመስተዳድር ምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይገኛል፡፡

2. Any head who specified in sub-article /1/ /c/ of this article shall have the obligation to take part in Administrative council meeting; the same cannot attend the meeting due to the reason beyond capacity, the Vice head or where there are more than one vice heads, vice head who has been specifically delegated by writing or in the absence of vice head who has been specifically deligated by writing, the Vice head who has priority in delegation shall take part in the meeting of the Administrative Council.

## 6. የርዕሰ መስተዳድሩ ስልጣንና ተግባር

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር በተሻሻለው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 68 የተመለከተው ይሆናል፡፡

## 6. Powers and Duties of Chief Executive

The powers and duties of chief executive of the region shall be as specified under article /68/ of the amended constitution of southern Nations, Nationalities and peoples' Region;

## 7. የምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር በተሻሻለው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 69 የተመለከተው ይሆናል፣

## 7. Powers and Duties of Deputy Chief Executive

The powers and duties of deputy chief executive of the region shall be as specified under article /69/ of the amended constitution of southern Nations, Nationalities and peoples' Region.

## 8. የክልል መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር በተሻሻለው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 66 የተመለከተው ይሆናል፡፡

## 8. Powers and duties of Administrative council of the Region

The powers and duties of Administrative council of the region shall be as specified under article /66/ of the amended constitution of Southern National, Nationalities and Peoples region.

## 9. የመስተዳድር ምክር ቤት አሰራር

1) የመስተዳድር ምክር ቤት ፡-

ሀ/ የራሱ የውስጥ ደንብ ይኖረዋል፤

ለ/ በውስጥ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ያደርጋል፤

ሐ/ ምልአተ ጉባኤ የሚሟላው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ይሆናል፤

## 9. Procedure of Administrative council

1. Administrative council:-

a) have its own rules of procedure;

b) conduct ordinary and extraordinary meetings in accordance with its rules of procedure;

c) have a quorum where more than half of its members are present;

መ/ የሚያስተላልፈው ውሳኔ በተባበረ ድምጽ ይሆናል፤ በተባበረ ድምጽ መወሰን ካልተቻለ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል፡፡

2) **ርዕሰ መስተዳድሩ፡-**

ሀ/ የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣ ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይወስናል፤

ለ/ የመስተዳድር ምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል፤

ሐ/ ለመስተዳድር ምክር ቤቱ በአጀንዳ የቀረበ ጉዳይ በርዕሰ መስተዳድር ጽህፈት ቤት መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ካገኘው አጀንዳውን ለሌላ ጊዜ ሊያስተላልፍ ይችላል፤

d) pass decisions by consensus or, failing that, by majority vote.

2. **Chief Executive**

a) without prejudice to the rights of the members of the council of the administrative council to propose agenda, determine the agenda of the council;

b) preside over the meetings of the council;

c) adjourn the meeting under circumstances where he finds it necessary to refer a case in his office, included in the administrative councils agenda

## 10. የርዕሰ መስተዳድር ጽህፈት ቤት

1) የርዕሰ መስተዳድር ጽህፈት ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 70 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የርዕሰ መስተዳድር እና የመስተዳድር ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ሆኖ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 70 ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ የተመለከተው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕስ መስተዳድሩ ስልጣንና ተግባሩን ለማከናወን የሚረዱ ልዩ ልዩ ጽህፈት ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

## 10. Chief Executive Office

1. Office of chief executive shall be an office of chief executive and administrative council in accordance with sub-article /2/ article 70 of the amended regional government constitution, and shall have the power and duty prescribed in sub-article /4/ article 70 of the constitution;

2. Without prejudice the prescription under sub-article /1/ of this office, the president may establish various offices to implement his powers and duties. The details shall be decided by regulation.

## ክፍል አራት

## የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች ሥልጣንና ተግባር

### 11. የወል ስልጣንና ተግባር

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 መሠረት የመስተዳድር ምክር ቤት አባል የሆነ እያንዳንዱ የአስፈፃሚ አካል መሥሪያ ቤት በሥራው መስክ፡-

ሀ) ሕግና ፖሊሲዎች ያመነጫል፣ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣

ለ) ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ የአቅም ግንባታ ኘሮግራሞችን ተግባራዊ ያደርጋል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ እንደአስፈላጊነቱ ያሰራጫል፣

ሐ) የፌዴራልና የክልሉን ሕጐች በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

መ) በሕግ መሰረት ውሎችና ስምምነቶች ያደርጋል፣ ሠራተኛ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

ረ) የኤች አይ ቪ ኤድስ ተጠቂዎችንና የአካል ጉዳተኞችን የእኩል ተጠቃሚ እና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ያመቻቻል፣ ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ያመቻቻል፣

ሰ) በሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችንና የወጣቶችን ጉዳይ፣ የሕጻናት ጥቅምና ደህንነትን ያስጠብቃል፣ የአካባቢ ጥበቃን፣ የአደጋ ስጋት ስራ አመራርን፣ የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብር መካተታቸውን ያረጋግጣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል ፣

## Part four

## Pawer and Duty of Executive Organ Offices

### 11. Common Powers and Duties

1. Each executive organ office which are member of Administrative council, based on article /5/ of this proclamation, in its field of activity shall:-

a) Initiate Law and policies, prepare plans and budgets, and upon approval implement the same;

b) Undertake study and research, implement capacity building programmers, collect, compile and, if necessary, disseminate information;

c) Ensure the enforcement of federal and regional laws,

d) Enter in to contracts and agreements based on laws, recruit, administer and dismiss employee;

e) Facilitate the circumstance by which HIV Aids victims and disables to be equal beneficiary and full participant;

f) Ensure the incorporation of women and youths affair, environmental protection, and accident risk managements, human right action programmers in policies, laws, development programmers and projects.

2) በየአስተዳደር እርከን የሚገኙትን የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶችን እና በማቋቋሚያ ሕጐቻቸው ተጠሪ የሆኑ የአስፈፃሚ አካላት መስሪያ ቤቶችን አፈጻጸምበበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል ፣ አደረጃጀታቸው፣ የሥራ ፕሮግራሞቻቸ ውንእናበጀታቸውን መርምሮ ለሚመለከተ ው የመንግስት አካል እንዲያቀርቡ ይወስናል፣

3) ተጠሪው የሆኑ የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅቶችን አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ የልማቱ አጋዥ ሆነው መስራታቸውን ያረጋግጣል፤

4) በዚህ አዋጅና በሌሎች ህጎች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

5) ስለሥራው አፈፃፀም በየወቅቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ እና ለመስተዳድር ምክር ቤት ሪፓርት ያቀርባል፣

## 12. የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) የክልሉን የልማት ዕቅድ አዘገጃጀትና አፈፃፀም ሥርዓት ይዘረጋል፣ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የክልሉን የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት ዕቅድ ያዘጋጃል ሲፈቀድም ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

2) የክልል መንግስት በጀት ያዘጋጃል፣ በተፈቀደው በጀት መሰረት ክፍያ ይፈፅማል፣ የበጀቱን አፈፃፀም ያስተዳድራል፣ ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፣

2. head and coordinate the performances of the executive organs' offices which are accountable to it under the laws establishing them and executive body organizations found under different administer hierarchy; review the organizational stricture, work programs and budgets and approve their submission to the appropriate government bodies;

3. Follow-up and support the development enterprises of the regional government made accountable to it in accordance with the relevant law, and ensure that they operate as development catalysts;

4. Exercise the powers and duties given to it under this proclamation and other laws;

5. Submit periodic performance reports to the President and Administrative council.

## 12. Finance and Economic Development Bureau

The Bureau shall have the following powers and Duties

1. Lay down the region development plan preparation and execution procedure, prepare the region's economic and social development plan through coordinating the concerning organs and implement when permitted;

2. Prepare budget, and execute pay in accordance with the budget; administer, evaluate and supervise the execution of the budget;

3) የክልሉ መንግስትን የበጀት፣ የሂሳብ፣ የክፍያና፣ የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፣ በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣

4) የክልሉን መንግስት የገንዘብ ሰነዶች፣ ገንዘቦችና ንብረቶች ይይዛል ያስተዳድራል፣

5) የክልሉን መንግስት የብድርና ዕርዳታ ስምምነቶች ይፈርማል፣ ያስተዳድራል፣

6) ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማትና ዕድገት የሚረዱ ጥናቶችን ያደርጋል ያሰራጫል፣

7) በኢኮኖሚና ማሕበራዊ ልማት ዘርፍ የተሰማሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ስራ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

8) የክልሉን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት መረጃዎችን ይሰበስባል ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፣

9) የክልሉን የፊዚካልና ማህበራዊ መሰረተ-ልማት ስርጭትና የተፈጥሮ ሀብት የሚያሳይ ካርታና አትላስ ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣

10) ዘመናዊ የበጀት አስተዳደር የሂሳብ አያያዝ፣ የግዥና የንብረት አስተዳደር ስርዓት ይመሰርታል፣ ስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣

11) የክልሉን መንግስት የፋይናንስና ንብረት ኢንስፔክሽን ያከናውናል፣ እርምጃ ይወስዳል እንዲወስድም ያደርጋል'

12) የክልሉን የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፣

13) የክልሉን መንግስት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ያሳትማል፣ ያሰራጫል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል

14) የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ህጎች ላይ ማብራሪያ ያዘጋጃል ያሰራጫል፣

15) ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

3. Lay down procedures of budget, account, pay and internal audit of the regional state and follow up the implementation;

6. Keep and administer treasury bills, moneys and properties of the regional state;

7. Sign and administer loan and donation agreements of the regional state;

8. Conduct studies fostering the economic and social development and growth and distribute thereof;

9. Coordinate and supervise the activities of governmental and non-governmental organization with the concerning bodies who are engaged in economic and social development sectors;

10. Collect, organize, analyze, and distribute the social and economic development information of the region;

11. Prepare and distribute map and atlas that show the physical and social infrastructure distribution and natural resources of the region;

12. Establish modern budget administration, accountancy, purchase and property administration procedure, supervise the application thereof;

13. Undertake finance and property inspection activity of the regional state, take measures and cause to take measures;

14. Lead and coordinate the demographic affair of the region;

15. Publish, distribute, follow up and supervise income collection receipts of the regional state;

16. Prepare briefings on the finance and economic development laws and distribute there of;

17. Perform other activities to achieve the objective.

13. የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) ለአርሶ አደሩ፣ ለአርብቶ አደሩና ለግል ባለሃብቱ የሚሰጡ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ቀልጣፋና ጥራት ያለው፣ ተደራሽና ውጤታማ እንዲሆን ስርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፣

2) የግብርና ልማት በገበያ እንዲመራ ያደርጋል፣ ለገበያ የሚመረቱ የግብርና ምርቶች እንዲስፋፉና የጥራት ደረጃው እንዲሻሻል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

3) የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ የሚጠይቀውን የሰለጠነ የሰው ሃይል ለሟሟላት ከሚመለከታቸው የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሠራል፣

4) የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማትን ለማስፋፋትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማፋጠን የሚያስችሉ የግብርና ቴክኒክና ሙያ፣ ትምርትና ስልጠና ተቋማትን፣ የግብዓት ማባዣ ማዕከላት፣ የማሰልጠኛና ሰርቶ ማሳያ ማዕከላት፣ ላብራቶሪዎችና ሌሎች ተቋማት ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣ ይመራል፣

5) የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት ያስፋፋል፣ የምርት ጥራት እንዲረጋገጥ ይሠራል፣ የገበያ መሠረተ ልማት እንዲገነባ ያደረጋል፣ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፣ ይቆጣጠራል፣

6) በክልሉ የግብርና ምርምር አቅም ይገነባል፣ የምርምርና ስርፀት ሥርዓት ይዘረጋል፣ የባለድርሻ አካላት በቅንጅትና በትብብር እንዲሠሩ ያስተባብራል፣ ይመራል፣

**13. Agriculture and Natural Resources Development Bureau**

The Bureau shall have the following powers and Duties:-

1. Lay-down a system to make the extension service which is provided for peasant, pastorial and private investor to be effective, quality, accessable and efficient; implement the same;
2. Make agricultural product to be led by the market and lay-down a system that enables to expand agricultural products which produced for the market and to improve its quality level; follow-up its accomplishment;
3. Work in integration with the concerned educational institution in order to fulfill professionals that agricultural and natural resource development sectors need;
4. Establish agricultural technical and vocational, educational and training institution, input multiplication center, training and display center, laboratory and other institution to expand agriculture and natural resource development and to swift technology transform; head and administer the same;
5. Expand coffee, tea and spices work to ensure product quality, make to build market infrastructure, devise modern transaction system; implement and control thereof;
6. Build capacity of agricultural research, stretch out research and awareness system, coordinate and head stakeholders to work in coalition and coordination;

7) የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ግብዓቶች ብዜት፣ አቅርቦትና ስርጭት፣ የግብይት፣ የዝውውርና የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይመራል፣ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣

8) ምርታማነቱ ያደገ፣ የምርት ብክነት የቀነሰና ጥራቱ የተጠበቀ የዘመናዊ ግብርና ልማት ለመገንባት የግብርና ሜካናይዜሽን ያስተዋውቃል፣ አቅርቦቱን ይደግፋል፣ ያስፋፋል፣

9) የዕጽዋት በሽታዎች፣ ወረርሽኝና ተዛማች ተባዮችን እንዲሁም አደገኛና መጤ አረሞችን የመከላከያና የመቆጣጠሪያ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ሲከሰትም አፋጣኝ እርምጃ ይወስዳል፣

10) የእጽዋትና የአዝርዕት ላይ የኳራንቲን ቁጥጥር ያደርጋል፣ የጥራት ማረጋገጫ ይሰጣል፣

11) ዘላቂ የግብርና ልማትን ለማረጋገጥ የተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራዎችን ያጠናል፣ ዲዛይንና የልማት እቅድ ያዘጋጃል፣ በህዝብ የላቀና የተደራጀ ተሳትፎ እንዲተገበር ይሠራል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፣

12) የጥቃቅንና የአነስተኛ መስኖ ግንባታ እንዲስፋፉ ይሠራል፣ የቴክኖሎጂ አማራጭ ለየታና አቅርቦቱንም ይደግፋል፣

13) የመሬት መርታማነት ለማሻሻል የአፈር ንጥረ ነገር ይዘት ምረመራ ያካሂዳል፣ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ፓኬጆችን እንዲቀረጹ ያደርጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

14) በገጠር ለምግብ ዋስትና ችግር የተጋለጡ አካባቢዎችንና የኅብረተሰብ ክፍሎችን ይለያል፣ መንስኤውን ያጠናል፣ ይደግፋል፣ በዘርፉ የሚሠሩ ባለድርሻ አካላትን ያስተባብራል፣

7. Lay-down a procedure for agricultural and natural developlment inputs multiplication, supply and dissemination, marketing, transfer and quality control; lead thereof and offer competence assurance;

8. Introduce agricultural mechanization to build modern agricultural development of which productivity grown, reduce product wastage and keep quality, support and enlarge the supply;

9. Stretch out protecting and controlling procedure of plant disease, outbreak and transmittable pests and dangerous and new-coming weeds, take urgent measure upon appearance;

10. Carry out quarantine control on plants and crops ; grant quality assurance;

11. Undertake study for coordinated natural resource development and conservation to ensure sustainable agricultural development, prepare design and development plan; work, coordinate and lead the same to be carried out with better and organized public participation;

12. Work to expand the construction of micro and small irrigation, and identify technology alternatives and support supply;

13. Carry out research of soil ingredient content to improve land productivity, cause to frame work package of fertile land improvement, follow-up its implementation,

14. Identify, study the cause and support environments and parts of community which exposed to food insecurity in rural area; coordinate and head stake holders who work in similar sector;

15) በክልሉ በሰው ሰራሽ ወይም በተፈጥሮ የሚከሰት አደጋ ለመከላከል የሚያስችል የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አደጋ ሲከሰትም ፈጣን ምላሽ ይሰጣል፣ ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ያስተባብራል፣ ይመራል፣

16) የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲቋቋሙ፣ እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ ይሰራል፣ ይደግፋል፣

17) የገጠር መሬት በባለቤትነት ያስተዳድራል፣ የአጠቃቀምና የአስተዳደር ሥርዓትን ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

18) በገጠር ለኢንቨስትመንት ወይም ለሰፈራ ወይም ለሌሎች አገልግሎቶች መሆን የሚችሉ መሬቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጥናት ይለያል፤ ካርታ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፣

19) በገጠር ለመንግሥትና ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታውን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲለቅ የሚደረግ የገጠር መሬት ባለይዞታ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካሳ የሚከፈለበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

20) በግብርና ልማት ኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የቴክኖሎጂ አቅርቦትና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ ይሰጣል፤ ከአርሶ አደሩ ጋር በምርትና ግብይት የሚተሳሰሩበት ሥርዓት ይዘረጋል፣

21) ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

15. Lay-down precaution information system that enable to protect natural and man-made disaster in the region, give immediate response upon the appearance of the disaster, and coordinate and lead other stake holders;

16. work and support that cooperative association to be established, strengthen and expanded;

17. Administer ownership of rural land; devise, cause to accomplish, follow-up and control administration and usage system;

18. identify through study lands for investment, settlement and other services with concerned body in rural area, prepare and transfer map to the concerned body;

19. devise asystem, based on relevant law, to pay compensation to the owner of rural land who displaced from his holding either fully or partial for the benefit of government and public, follow-up and supervise its accomplishment;

20. offer a support on technology supply and extension service to those investors who take part on agricultural development investment, lay-down a procedure by which they intertwine with farmers on production and marketing;

21. perform other activities to achieve the objective;

## 14. የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) ለአርሶ አደሩ፣ ለአርብቶ አደሩና ለግል ባለሃብቱ የሚሰጡ የዘርፉ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ቀልጣፋና ጥራት ያለው፣ ተደራሽና ውጤታማ እንዲሆን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣
2) ዘርፉ የሚጠይቀውን የሰለጠነ የሰው ሃይል በትምህርት ዝግጅትና በሙያ መስክ በጥናት ይለያል፣ ከሚመለከታቸው የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሠራል፣
3) በምርታማነታቸውና በሽታን በመቋቋም የታወቁ የሀገረሰብና የውጭ ዝሪያ ያለቸው እንስሳትን ይለያል፣ የዝርያ ማሻሻያ ሥራ ይሠራል፣ ያስፋፋል፣
4) በየደረጃው አስፈላጊ የሆኑ አደረጃጀቶች፣ ማሰልጠኛና ሠርቶ ማሣያ ማዕከላት፣ የህክመና መስጫ ተቋማት፣ ላብራቶሪዎችና ሌሎች መሠረተ ልማቶች ያቋቁማል፣ የአስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስተዳድራል፣
5) የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት በገበያ እንዲመራ ያደርጋል፣ የእንስሳትና አንስሳት ተዋጽኦ ምርቶች ምርታማነትና የጥራት ደረጃ እንዲሻሻል ይሠራል፣ ቅድመና ድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች ያስተዋውቃል፣ አቅርቦቱን ይደግፋል፣ ያስፋፋል፣
6) በክልሉ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት የምርምር አቅም ይገነባል፣ የምርምርና ስርፀት ሥርዓት ይዘረጋል፣

## 14. Animals and Fish Resource Bureau

The Bureau shall have the following powers and duties;

1. Laydown a procedure to make the sector's extension service which is given to farmers, pastorials and private investor to be efficient, quality, accessable and productive, put the same into practice;
2. Identify through study the trained human power by education preparation and vocational field that the sector demands, work in collaboration with concerning education and training institutes;
3. Identify those animals, which are known by their productivity and resistance of disease, have the species of homeland and oversea, undertake and expand activities of species improvement;
4. Establish, at each level the necessary, structures, training and display center, institutions of clinical sale, laboratories and other infrastructural; lay dawn administration procedure and manage there of;
5. Make animals and fish resource development to be lead by the market, work to improve the quality level of animals and animals product productions and productivity; introduce pre- and post-production technology, support and expand supply;
6. Build the capacity of animals and fish resource research, stretch out system of research and awarness in the region;

ashamlaws.wordpress.com

7) የእንስሳትና ዓሣ ምርትና ምርታማነት ማሳደጊያና ማሻሻያ ግብአቶች አቀርቦትን ያመቻቻል፣ እንዲመረቱ ያደርጋል፣ በዘርፉ የሚሰማሩ አካላትን አቅም ይገነባል፣ የብቃት ማረጋገጫ ይሠጣል፣ ይሰርዛል፣

8) የእንስሳት ክትባትና መድሐኒት አቅርቦት፣ ግብይት፣ አያያዝ ዝውውር ስርዓት ይዘረጋል፣ የብቃት ማረጋገጫ ይሠጣል፣ ይቆጣጠራል፣ በህግ መሠረት እርምጃ ይወስዳል፣

9) የእንስሳት ገበያና የዝውውር መስመሮችን ይወስናል፣ ይቆጣጠራል፣ የኳራንቲይን አገልግሎት ይሰጣል፣ ከአጎራባች ክልሎችና ከፌዴራል መንግሥት አካላት ጋር በቅንጅትና ትብብር ይሠራል፣

10) የእንስሣት በሽታ ወረርሽኝና ተዛማች በሽታዎች እና የውሃ አካላት ብክለት የመከላከያና የመቆጣጠሪያ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፣ ሲከሰትም አፋጣኝ እርምጃ ይወሰዳል፣

11) የእንስሳት የጤና አገልግሎት ይሰጣል፣ የእንስሳት በሽታዎች ምረመራ፣ አሰሳና ቁጥጥር ሥራዎችን ያካሄዳል፣

12) በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ ባለሀብቶ የቴክኖሎጂ አቅርቦትና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ ይሰጣል፣ ከአርሶ አደሩ ወይም አርብቶ አደሩ ጋር በምርትና በግብይት እንዲተሳሰሩ ይደግፋል፣

13) የእንስሳትና ዓሳ ሀብት በልማት ቀጠናዎች ይለያል፣ እንዲለማ ተገቢውን ድጋፍ ያደረጋል፣

7. Facilitate the supply of inputs for growth and improvement of animals and fish product and productivity, cause the same to be produced, build the capacity of those who take part in the sector; certify and cancel competence assurance;
8. Lay down a system of handling, marketing, supply and transfer of medicine and animal vaccination, certify and control competence assurance, take measure based on the law there of;
9. Decide and control animals marketing and transaction lines; offer quarantine service; work in integration and collaboration with federal government and neighboring regions;
10. Lay-down controlling and prevention system of outbreaks of animals' disease and related disease and contamination of water body; cause to implement the same; take urgent measure upon appearance;
11. Give animals health service; carry out diagnoses; assessment and supervision of animal diseases;
12. Support in supply of technology and extension service to those investors who participate in animals and fish resource investment, support the investor to intertwine with farmers and pastorials;
13. Identify animals and fish resource interims of development section; make the relevant support for development;

14) ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

15. የአርብቶ አደር ጉዳይ ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) በአርብቶ አደሩ አካባቢ የተቀናጀ ተከታታይ ልማት ለማካሄድና የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚረዱ ሥራዎችን ያከናውናል፣
2) በአርብቶ አደር አካባቢ የሚከናወኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ኘሮግራሞችንና ኘሮጀክቶችን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣
3) የአርብቶ አደር የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራምን ያቅዳል ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን ያከናውናል ፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ኘሮግራሙን በበላይነት ይመራል፣ ይደግፋል፣ ያስፈጽማል፣
4) የአርብቶ አደር አካባቢዎች የማስፈፀም አቅም ለማሳደግ የሚረዱ ተግባራት ታቅዶ እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡ ጠቃሚ ልማዶች እንዲጐለብቱ ፣ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለማስወገድ የሚያስችሉ ተግባራትን ከሚመለከተው አካል ጋር ተባብሮ ይሰራል፣
5) በአርብቶ አደር አካባቢ ልማት ማስፈፀሚያ የሚውል ፈንድ ከመንግሥት ወይም ከአጋር ድርጅቶችና ከህብረተሰቡ እንዲገኝ ያስተባብራል፣ሲገኝም ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣
6) በአርብቶ አደር አካባቢ ሕዝቦች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር እንዲጠናከር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ የልማት ሥራዎችን ያከናውናል፣
7) ለአርብቶ አደሩ አካባቢ ሥነ-ምሕዳር ተስማሚ የሆነ የምርት ማሳደጊያ ቴክኖሎጂዎች እንዲቀርቡ ያስተባብራል፣ ይፈጽማል፣
8) በአርብቶ አደሩ አካባቢ የመሠረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ሠጭ ተቋማት ያካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ እንዲዘረጉ ያደርጋል፣

14. Perform other functions to achieve the objective

## 15. Pastoralist Affair Bureau

The Bureau shall have the following powers and duties

1. Carry out activities that help to undertake coordinated sustainable development and ensure food security in pastoral areas;
2. Coordinate, implement and cause to implement the social and economic development programs and projects undertaken in pastoral areas;
3. Plan settlement program of pastorals, carry out function of awareness creation, head, support and cause to implement the same in coordination with the concerned body;
4. Plan and make to accomplish activities that help to enhance the execution capacity of pastoral areas. Work in cooperation with concerning bodies for useful practices to be developed and to eradicate harmful practices;
5. Coordinate to get fund from government, non-governmental organization, and from the public for the execution of development in pastoral areas, and put into practice the same;
6. Undertake various developmental activities in cooperation with concerned bodies to reinforce the social and economic relations among the peoples around pastoral areas;
7. Coordinate those production increment technologies that suit the ecology of the areas to be supplied to pastoral areas and execute same;
8. Undertake activities toward infrastructure and social service delivering institutions to be established in pastoral areas taking in to account the statsquo of the areas;

9) በአርብቶ አደሩና በከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢ መንግስታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚሠሩ የልማት ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ አርብቶ አደሩ ከልማት ስራዎቹ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

10) ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## 16. የውሃና መስኖ ልማት ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) የክልሉን የውሃ ሀብት ያስተዳድራል፣

2) የክልሉን የከርሰ ምድርና ገፀ ምድር ውሃ ሀብት በመጠንና በጥራት ይለያል፣ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

3) የውሃ ልማትና አስተዳደር ማኑዋሎችንና ደረጃዎችን ያዘጋጃል እንዲሁም ሌሎች የውሃ ሴክተር ስራዎችን ይቆጣጠራል፣

4) የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ዝርዝር ጥናት ያጠናል፣ ግንባታዎችን ያከናውናል፣

5) የከተማና ገጠር የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን እንዲያድግ ያደርጋል፣ ደረጃውን ይወስናል፣ የቴክኒካዊ ሥራዎችን አፈፃፀም ይከታተላል፣

6) የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማት አስተዳደር ኮሚቴዎችን ያደራጃል ሕጋዊ የሰውነት ፈቃድ ይሰጣል፣ የከተማ ውሃ አገልግሎት ድርጅቶችን ያደራጃል፣

7) በክልሉ የውሃ ተፋሰሶች ፍትሐዊና ሚዛናዊ የውሃ ክፍፍልና ምደባ መኖሩን ይቆጣጠራል፣

8) የውሃ ዕጥረት ባለባቸው የክልሉ አካባቢዎች የአስቸኳይ ጊዜ የውሃ አቅርቦት ያመቻቻል፣ ችግሩንም በዘለቄታዊነት ለማስወገድ የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፣

9. Coordinate, follow up and provide support to development activities undertaking by government and non-governmental organizations in pastoral and semi- pastoral areas; facilitate the conditions from which the pastoral to be beneficiary;

10. Accomplish other necessary activities to achieve the objective.

## 16. Water Resource Bureau

The Bureau shall have the following powers and duties.

1. Administer the water resource of the region;
2. Identify interms of amount and quality of inner core and outer core water resource in the region, facilitate the condition to use the same;
3. Prepare water development, and administration manuals and standards as well as supervise the activities of the water sector;
4. Conduct detail studies on the supply of potable water and undertake constructions;
5. Undertake activities to develop the supply of pure water to urban and rural areas, determine the standards, and follow up the execution of technical activities;
6. Organize rural potable water institution administration committees, grant license of legal personality and organize urban water service organization;
7. Supervise the presence of fair and balanced drainage water distribution and allocation in the region;
8. Facilitate the supply of emergency water in areas where shortage of water exist, and carry out activities enable to solve the problem in sustainable manner;

9) የውሃ አካላት ብክለትን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ የውሃ ናሙና ይሰበስባል፣ የላብራቶሪ ምርመራ ያደርጋል፣

10) በውሃና በመስኖ ልማት ስራ ለሚሰማሩ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለሞያዎች ደረጃቸውን ይወስናል፣ የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣

11) የክልሉን የመስኖ ልማት ሽፋን ለማሳደግ የመስኖ ልማትና የማጠንፈፍ ሥራዎች ጥናትና ዲዛይን ያከናውናል፣ የግንባታ ጨረታ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

12) የወንዞች ፍሰት አቅጣጫ መግራት እና የጐርፍ መከላከያ ሥራዎች ጥናት ዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥር ሥራዎችን ያከናውናል፣

13) በክልሉ የመስኖ አለኝታ ጥናት ያካሂዳል፣ የመካከለኛና ከፍተኛ የመስኖ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች መስፈርት ያዘጋጃል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ተግባራዊነቱን ይመራል፣

14) የመስኖ ተቋማትን ይንከባከባል፣ ይጠግናል፣ የአስተዳደር ሥርዓቱን የዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

15) የማዕድንና ኢነርጂ ልማት እና አስተዳደር ሥራዎችን በበላይነት የመራል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስተባብል፤

16) ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

17. **የንግድና የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፣

2) በክልሉ ውስጥ ንግድን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ቀልጣፋ የግብይት ሥርዓትና ተገቢ የንግድ አሠራር እንዲሰፍን ያደርጋል፣

9. Prevent and supervise the pollution of water bodies, collect samples of water and undertake laboratory experiment;

10. Determine the standards for those contractors, consultants and professionals who take part on water and irrigation activity; grant, renew, ban and cancel license;

11. Research and design irrigation development and drainage so as to broaden the region's irrigation development coverage; prepare construction bid and implement;

12. Manage drainage system of rivers and perform activities regarding to the study, design and construction supervision of flood actions;

13. Condut irrigation security study; prepare, follow-up and supervise standards for medium and higher irrigation construction design and construction works, head its implementation;

14. Care and repair irrigation institutins and lay down administration procedures; follow up its implementation;

15. Head, supervise and coordinate works of mine and energy development and administration;

16. Implement other activities that help to achieve the objective.

**17. Trade and industry development Bureau**

The Bureau shall have the following powers and duties:-

1. Create conducive circumistances to expand trade, industry and investment;
2. Maintain efficient marketing systems and fair trade practices to promate and strength regional trade;

3) አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፣ የንግድ መዝገብ ያደራጃል፣

4) ተገቢ ያልሆነ የንግድ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችል የተሟላ ሥርዓት ይዘረጋል፣ የንግድ ሕጎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣

5) በሕግ መሰረት ለሸማቾች ጥበቃ ያደርጋል፣ የንግድ እቃዎችንና አገልግሎቶችን ሥርጭት ይቆጣጠራል፣

6) አግባብ ባለው አካል የዋጋ ቁጥጥር የተደረገባቸውን መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መተግበራቸውን ይቆጣጠራል፣

7) አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፤ ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ ይወስዳል፤

8) የሀገሪቱን ሕጋዊ ሥነልክ ሥርዓት በአግባቡ መተግበሩን ይቆጣጠራል፣

9) የንግድና የኢንዱስትሪ፣ የዘርፍና የሙያ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፣

10) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13/5/ የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የግብይትን ሥራዓትን በበላይነት ይመራል፣ የገበያ መሰረተ ልማት ስፋፋል፣ የምርት ጥራት ቁጥጥር ያደርጋል፣የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ ይከታተላል፣ በህግ አግባብ እርምጃ ይወስዳል፣

11) ለኢንቨስተሮችና በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሚሰማሩ ባላሀብቶች ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ሁሉንም አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

12) ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የኢንዱስትሪ መንደሮች የሚለሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው ያደርጋል፤

13) በክልሉ የካይዘን ፍልስፍና አስተሳሰብ ያሰርጻል፣ ውጤታማ እንዲሆንም ተቋማዊ ድጋፍ ይሰጣል፤ ክትትል ያደርጋል፣

14) በክልሉ የማኑፋክቸርንግ ኢንዱስትሪ እንዲፋጠንና በሂደትም የኢኮኖሚ መሪነት ቦታ እንዲያዝ ስትራቴጂ ይቀይሳል፣ ይመራል፣ ለኢንዱስትሪ ልማት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

15) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**3.** Offer, supervise and cancel business registration and licensing services based relevant law, and organize trade records;

**4.** Lay-down strategies that enable to protect unlawful trade and verify the respection of trade; follow-up the executions;

**5.** Make a protection to purchasers and control the dissemination of trade materials and services based on the law;

**6.** Supervise the implementation of basic trade commodities and services on which price contol has been undertaken by relevant body;

**7.** Control the fulfillment of standards of trade materials and services which have compeling Ethiopian level; take measure on those found below the set standards;

**8.** Control the appropriate implementation of legal standards of the country;

**9.** Encourage association of trade and industry, sector and profession to be established; strengthen those that have already been established;

**10.** Without prejudice the statement in subarticle /5/ of article 13 of this proclamation, Head trade practices, expand market infrastructure, supervise product quality, grant competence assurance and take measure with relevant law;

**11.** Create conducive conditions to those investors who participate in manufacturing sector and investors, give support; facilitate the circumistance to provide all services one stop-shop service;

**12.** Facilitate the enhancement of industry zones in collaboration with stakeholders; make infrastructure to be fulfilled;

**13.** Inculcate kaizen philosophy in the region; provide institutional support follow-upto make there of effective;

**14.** Devise and head a strategy to fasten manufacturing industry in the region and make it through time to hold the position of heading the economy; create favorable environment for the industry;

**15.** Perform other duties to achieve the objective.

## 18. የከተማ ልማት እና ቤቶች ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) የከተማና የገጠር ትስስር እና የከተሞች የእርስ በርስ ትስስር እንዲጠናከር ስትራቴጂ ይቀይሳል ተግባራዊ ያደርጋል፣

2) አግባብ ባለው ሕግ የክልሉን የከተማ መሬት አስተዳደር ሥርዓትን ያስፈጽማል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣የከተማ መሬት አቅርቦትና አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

3) የከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራምን በባለቤትነት ያስተባብራል፣ ከሚመለከታቸውም አካላት ጋር በመቀናጀት ይደግፋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ ዘላቂነት ካለው የልማት ተግባር ጋርም ያስተሳስራል፣

4) የከተሞችን የደረጃ መመዘኛና ደረጃ ይወስናል፣ ዕውቅና እንዲያገኙ ያደርጋል፣

5) ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፣

6) የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት እና ከድህነት ቅነሳ ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናት ያደርጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያግዛል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፣

7) በከተሞች ዘመናዊ መሰረተ-ልማት እንዲስፋፋ ጥረት ያደርጋል፣ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል የለማ መሬት ያዘጋጃል፣

8) የክልሉን ከተሞች ፕላን ያዘጋጃል፣ አተገባበራቸውን ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፣

9) በከተማ ፕላን ዝግጅት ለሚሰማሩ አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል ደረጃቸውን ይወስናል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይሰርዛል፣

10) ከተሞች የሚያመነጯቸውን ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች የሚወገድበትንና ውበት ያላቸው የመናፈሻ አገልግሎቶች የሚመሰረቱበትን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣

## 18. Urban Development and Houses Bureau

The Bureau shall have the following powers and duties:-

1. Devise and implement strategy in order to strengthen interrelation of urban and rural and internatation among urban;
2. Cause to implement, follow-up and supervise urban land administration system of the region based on relevant, lay down urban land provision and administraton system;
3. Coordinate the urban food security program as owner , support in integration with the concerned body and implement thereof, inter woven the same with sustainable development activity;
4. Determine on standards and grades of urbans, and cause to get recognition;
5. Provide integrated support to urban areas to be center of development to their surroundings;
6. Make a study regarding the conditions to undertake urban development together with rural development and poverty reduction in a coordinated manner, give hand to be implemented and follow-up its performance;
7. Strive to expand modern infrastructure in urban centers and make ready fertile lands that may use for various purpose;
8. Prepare urbans plan of the region, follow-up and support the implementation thereof;
9. Grant certificate of competence to those consultants to engage in urban plan preparations, determine their standard, grant license and cancel;
10. Lay-down working procedure for the establishment of disposal of garbage and sewerages generated from urban centers and attractive recreational services and provide support thereof;

11) በከተሞች ለሕዝብ ልማት ሲባል ለመንግስታዊ ፕሮጀክቶችና ለሌሎች አገልግሎቶች ለሚዛወሩ ይዞታዎችና ከይዞታቸው ለሚፈናቀሉ ሰዎች ካሳ የሚከፈልበት ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል አፈፃፀሙን ይከታተላል፣

12) ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ የለማ መሬት ያዘጋጃል፣ ለተገልጋይ ያቀርባል፣ የአቅርቦቱን ፍትሐዊነት ያረጋግጣል፤ የተላለፈ መሬት ህጋዊነቱን ተከትሎ ለልማት መዋሉን ይከታተላል፣ ህገ-ወጥ ግንባታዎችን ይቆጣጠራል፣ ህጋዊ ሥርዓትን ያስይዛል፤

13) የመሬትና የንብረት ዋስትና ካሳ ሥርዓት ይዘረጋል፣

14) በቴክኖሎጂ የተደገፈና ወጥ የሆነ የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና የአድራሻ መረጃ ሥርዓት በክልሉ ይዘረጋል፣

15) በከተሞች የልማትና መልካም አስተዳደር ሥራዎች ላይ ነዋሪው ህዝብ በተደራጀ አግባብ እንዲሳተፍ ለማስቻል የአሠራር ስርዓት ይዘረጋል፣ የማስፈጸም አቅም ይገነባል፤ ያስተባብራል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል::

16) በክልሉ የሚካሄደውን የቤቶች ልማት ፕሮግራሞችን ይመራል፣ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠነ የመኖሪያ ቤት እንዲሰራ ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

17) በከተማ ስራ አጥ ዜጎች በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ፕሮግራም ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ያደራጃል፣ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

18) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፣

11. Make to lay-down procedures of compensation payment to those holdings to be transferred and displaced from their holdings for the sake of public development, state projects and other services in urbans; follow-up the implementation thereof;

12. Prepare and provide to customer fertile land which stay for various services; ensure the fairness of the provision; follow-up that the land used for development; supervise illegal building and make the same to keep legal procedure;

13. Stretch-out compensation system for collateral of land and property;

14. Lay-down a system to record holding of urban land and information address which supported by technology in the region;

15. Lay-down a procedure to enable the residences to takepart on urban development and good governance in integration manner; coordinate and follow-up the performance;

16. Lead housing development programs to carry out in the region , offer technical support and supervise the same, devise a means through which the urban residences to build living house in line with their capability; follow-up its implementation;

17. Facilitate and organize the conditions on which urban unemployments to participate and use micro and small enterprise program; cause them to get support;

18. Carry out other related activities to implement the objective;

## 19. የኮንስትራክሽን ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) የፌዴራልና የክልሉ መንግስት የግንባታ ኮዶች፣ ስታንደርዶችና ሕጎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ የዲዛይንና የግንባታ ሥራዎችን ደረጃ ይወስናል፣
2) በግንባታ ዘርፍ ለሚሰማሩ የምህንድስና ባለሙያዎች፣ አማካሪዎችና ሥራ ተቋራጮች ይመዘግባል፣ የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፣
3) በክልሉ መንግስት ለሚገነቡ ሕንፃዎች የዲዛይንና የግንባታ ውሎች ስለሚይዟቸው የውል ቃሎችና የቴክኒክ መመሪያ ያዘጋጃል፣ በተገባው ውል መሠረት የጥራት ደረጃቸው፣ የጊዜና የዋጋ ገደቦች ተጠብቀው መሰራታቸውን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ እርምጃ ይወስዳል፣
4) በክልሉ ለሚካሄዱ ግንባታዎች ዲዛይን ያዘጋጃል፣ የዋጋ ጥናት ያካሂዳል፣ የምህንድስና ግምት ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ውለታ ያስተዳድራል፣ የጥራት ቁጥጥር ያደርጋል፣
5) የኮንስትራክሽን ግብዓት በላቦራቶሪ እየተፈተሸ ለግንባታ አገልግሎት እንዲውል ያደርጋል፣
6) የክልሉን የኮንትራክሽንና የዲዛይን ሥራዎች ፍላጎት ያጠናል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
7) አግባብ ላለው አካል በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የኮንስትራክሽን ሥራ ደረጃዎች ያወጣል፣ መከበራቸውንም ይከታተላል፡፡
8) የኮንስትራክሽን ዘርፍን እንቅስቃሴ ይመራል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣

## 19. Construction Bureau

The Bureau has shall have the following power and duties:-

1. Ensure that construction codes, standards and laws of federal and regional government have been respected; decides level of deign and construction works;
2. Register those engineers, consultants and contractors who to deploy on construction sector; grant, renew and cancel professional assurance certificate;
3. Prepare technical directive and contractual words that are included in design and construction contracts for the buildings which to be build by regional government, control its implementation by keeping quality level, duration and price limit based on the contract; offer the necessary support and take measure;
4. Prepare design, conduct price study, estimation of engineering for the constrictions which are being curried out in the region, ensure its implementation, administer contract and make quality supervision;
5. Make that construction inputs to stay on building service upon examining by laboratory;
6. Study the need of construction and design works of the region, make the same to be implemented;
7. Without prejudice the power vested to relevant organ, issue standard of construction work and follow up their implementation
8. Head the activities of the construction sector, and follow-up its accomplishment;

9) በአማካሪዎች ወይም በሌላ አካላት ለሚሰሩ ዲዛይኖች የማወዳደሪያ ዝክረ ተግባር ያዘጋጃል፣ የአማካሪ ደረጃ ይወሰናል፣ የአማካሪዎችን ወርሃዊ የግንባታ ሂደት ሪፖርት ይገመግማል፣ የአገልግሎት ክፍያቸውን ያፀድቃል፣

10) በአማካሪዎች ወይም በሌላ አካል የተሰሩ ዲዛይኖችን ይመረምራል፣ ያፀድቃል፣ የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ሥራዎችን ያካሂዳል፣ክፍያዎችን ያፀድቃል፣

11) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና የቁጥጥር ሥራዎችን ያከናውናል፣

12) የዘርፉን የሰው ሀብት ልማትና ደረጃዎች ዝግጅት ሥራዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣ የሚመለከታቸውን አካላትም ያስተባብራል፣

13) በመንግስትም ሆነ በግል ተቋማት በህንፃ አዋጁ በተካተቱ እና ወደፊትም በሚካተቱ ከተሞች ለሚገነቡ ህንጻዎች ዲዛይን ይገመግማል፣ የግንባታ ፈቃድ እና የመጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል፣

14) የህንፃ ሹም ጽ/ቤቶችን ያደራጃል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ የግንባታ ግብአት ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን በጥናትና ምርምር ሥራው እንዲሳተፉ ያስተባብራል፣

15) በክልሉ የዲዛይንና የኮንስትራሽን ዘርፍ ለተሰማሩ አማካሪዎች፣ ኮንትራክተሮች እና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፣

16) በክልሉ ውስጥ በአማካሪነትና በኮንስትራክሽን ሥራ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት አቅማቸውን እንዲያሳድጉና በጥራትና በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያበረታታል፣ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣

17) በግንባታ ሥራ ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ግንባታዎች ጉልበት ተኮር እንዲሆኑ ያበረታታል፣

18) ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፣

9. Prepare competition action plan for designs which to be made by consultants and other bodies, decide consultant standards, evaluate the monthly building report of consultants, approve service fees;

10. Examine and approve designs done by consultants or other body; undertake activities of follow-up and supervision of construction and approve fees;

11. Perform activities of supervision and development of construction industry;

12. Implement functions of human resource development and standards preparation of the sector; coordinate the concerned bodies;

13. Evaluate the design of buildings of cities which are being included and to be included in construction proclamation by government as well as private institutions, grant construction license and usage license thereof;

14. Prepare, head and supervise offices of construction official; undertake study and research of construction inputs; coordinate higher educational institution participate on study and research works;

15. Work capacity building activities to those consultants, contractors and professionals who deployed on design and constructions sector in the region;

16. Encourage and make the necessary support to those small and micro association, which deployed on consultation and construction works in the region to enhance their capacity, to be competent on quality and in the market;

17. Encourage constructions to be labour oriented so as to create work opportunity in construction sectors;

18. Perform other duties that can help to implement its objective;

ashamlaws.wordpress.com

## 20. ትራንስፖርትና የመንገድ ልማት ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል

1) በክልሉ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ የትራንስፖርት አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣

2) የትራንስፖርት አገልግሎቶች አቅርቦት በተቀናጀ መንገድ እንዲፈፀምና የክልሉን የልማት ስትራቴጂዎች በተሟላ ሁኔታ እንዲያገለግል መደረጉን ያረጋግጣል፤

3) የትራንስፖርት አገልግሎቶች አስተማማኝና ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት እንዲዘረጋና ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

4) በሀገሪቱን የትራንስፖርት ፖሊሲዎች መሰረት በክልሉ በሚገኙ ውሃ አካላት ላይ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲስፋፋ ያበረታታል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል

5) በክልሉ የትራንስፖርት መሰረተ-ልማት አገልግሎት እንዲስፋፋ፣ እንዲሻሻልና እንዲጠገን ያደርጋል፣

6) የክልሉን የመንገድ ልማት ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ድረጃ ይወስናል፣ ያስተዳድራል፣ የዲዛይንና የግንባታ ጥራት ቁጥጥር ስራዎችን ያካሂዳል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

7) በከተማ ታክሲ አገልግሎት ለሚሰማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ በዘርፉ የሚቋቋሙ ማህበራትን ይመዘግባል፣ ስምሪት ይሰጣል፣

8) በክልሉ ለሚቋቋሙ የተሽከርካሪ ጥገና ጋራዦች፣ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማትና ለተሽከርካሪ አመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ተቋማት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፣

## 20. Transport and Communication Bureau

The Bureau shall have the following powers and duties:-

1. Make to expand regular and irregular transport services in the region;
2. Check the supply of the transport service to be implemented in coordinating manner and serve the regions development strategy in sufficient circumstance;
3. Cause to lay-down inspection procedure to ensure reliable and safe transport services and make the same to be implemented;
4. Encourage transport services to be expand in the water bodies that found in the region in accordance with relevant transport policies of the country grant, renew and call off license;
5. Undertake activities that the transport infrastructure services to be expanded, improved and mended;
6. Head, determine standard and administer road development activities as wellas carry out, follow-up and supervise the controlling activities of design and construction quality of the region;
7. Offer license to those individuals and enterprises which to deploy on city tax service; register and dissident the associations to bevestablished in the sector;
8. Certify, supervise and call off, when necessary, the license of maintenance garage, training institution of vehicles and institution of technical examination for vehicles annually;

9) በህዝብና በጭነት ማመላለሻ ሥራ ላይ ለሚሰማሩ አካላት የብቃትና የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤ ለሚሰጡት አገልግሎት የሚያስከፍሉትን ታሪፍ ያወጣል፣ ይከታተላል፤ ለህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችም ደረጃ ያወጣል፣ ያድሳል

10) ለአሽከርካሪዎችና ለተሽከርካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣

11) የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና እና የቴክኒሻኖች ማሰልጠኛ ማዕከላት ያቋቁማል፣ ስልጠና ይሰጣል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ያደርጋል፣

12) የሕዝብና የጭነት ማመላለሻ መናኸሪያዎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣ ያስተዳድራል፣

13) የመንገድ ትራንስፖርት ሕጎች መከበራቸውን ይከታተላል፣እርምጃ ይወስዳል

14) ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ላይ የሚለጠፉ ሰሌዳዎችንና የትራንስፖርት ህትመቶችን ያሳትማል፣ ያሰራጫል፤

15) በክልሉ የመንገድ ደህንነት ፈንድና ካውንስል ያቋቁማል፣

16) የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ሲከሰት ወይም በሌሎች አስፈላጊ ምክንያቶች የንግድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በአስፈላጊው ቦታና መስመር ደልድሎ ያሰማራል፣ ይከታተላል፣

17) ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የመንገድ ትራፊክ አደጋ ለመከላከል በቅንጅት ይሠራል፣

18) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፣

9. Grant, renew and call off professional and vocational license to those body who take part on public and lory transporting, issue tarrif and followup to the transportation service fee, and issue level and renew pulic transport vehicles;

10. Grant, renew, ban and cancel competence assurance of drivers and vehicles;

11. Establish training center of technicians and of evaluation the competence assurance of driver, train and make the same to be patronized with modern technology;

12. Establish and administer public and lory transportation station;

13. Follow-up that road and transport laws have been respected and take measure;

14. make to be printed and disseminate transport seal and board to engine vehicles;

15. Establish road safety fund and council in the region;

16. Deploy and follow-up trade transportation vechiles on the necessary place and line when natural and man-made disaster and temporary economic and social problems happen;

17. Work in collaboration with other stakeholders to prevent road traffic accidents;

18. Perform other related functions that enable to achieve the objective;

## 21. የገቢዎች ባለሥልጣን

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) የክልሉን የታክስና የገቢ አሰባሰብ ስርዓት በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

2) በክልሉ በመካሄድ ላይ ያለውን የታክስ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አፈጻጸም በባለቤትነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

3) ቀልጣፋ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ይዘረጋል።

4) ለታክስ ከፋዩ አማራጭ የታክስ መክፈያ ተቋማትን ያመቻቻል፤

5) ታክስ ከፋዮች በፍቃደኝነት ታክስ የመክፈል ባህልን እንዲያዳብሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ያደርጋል፤

6) በክልሉ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ተመስርቶ ጥናቶችን በማካሄድ የክልሉን የገቢ መሠረት ያሰፋል፣ በታክስ አስተዳደሩ የሚከሰቱ ችግሮች እንዲፈቱ ያደርጋል፣ የፖሊሲና የሕግ ሀሳቦችን ያመነጫል፤

7) የታክስ ሕጉችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ በማናቸውም ሰው እጅ የሚገቡ ሰነዶችን ይመረምራል፣ ይይዛል፤

8) የታክስ ህጉችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ይመረምራል፣ ይከሳል፣ ይከራከራል፣ ይህንኑ ለማከናወን የራሱን ዐቃቢያነ-ህግና መርማሪዎችን ያደራጃል፣ ተግባራቸውንም ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

9) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣኑን በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ለክልል ፍትህ ቢሮ ወይም ለቢሮው የስር መዋቅሮች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

## 21. Revenues Authority

**The authority shall have the following power and duties:-**

1) Lead and administer the region's tax and re collection system;

2) Head and co-ordinate the implementation of the 's tax system reform program undertaken in the regior

3) Establish efficient, transparent, and accountable s delivery system;

4) Facilitate the alternative tax paying center for tax pa

5) Implement awareness creation programs to prom culture of voluntary compliance of tax payers i discharge of their tax duties;

6) Conduct research based on the economic activities region to expand the revenue mechanisms of the r resolve tax administration problems, initiate polic law;

7) Investigate and seize documents under the possess any person that are required for the enforcement laws;

8) Investigate, prosecute and litigate tax offences fo discharge of such responsibilities, organize its prosecution and investigation units; lead and sup their performance;

9) Without prejudice to the provision under sub-arti this article, the Bureau may, specific matters investigation and prosecution power, deligate to J Bureau of the region and to bureaus of inside stru by ;

ashamlaws.wordpress.com

10) ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉት መረጃዎች ያሰባስባል፣ ያጠናክራል፣ እነዚህኑ በመጠቀም ታክስ ይወስናል፣ ይከሳል፤

11) ታክስ ያልሆኑ የከተማ ቦታ ይዞታ፣ የቤት ባለቤትነት፣ የንብረትና የአገልግሎት ክፍያ አወሳሰንና አሰባሰብ የሚያገለግሉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

12) ከተሞች የማዘጋጃ ቤቶች ገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ጥናት ያደርጋል፣ ገቢዎችን በሕጉ መሠረት ይሰበስባል፣ ለመንግስት ግምጃ ቤት ገቢ ያደርጋል፣

13) የታክስ ወይም የግብር ግዴታቸውን ያልተወጡ የግብር ወይም የታክስ ከፋዮችን ንብረት በህግ መሠረት ያስከብራል፣ ያስይዛል፣ በሃራጅ እንዲሸጥ ያደርጋል፣

14) በታክስ እና በግብር ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ይመረምራል፣ ውሣኔ ይሰጣል፣ መቀጫዎችን በሕግ መሠረት ይጥላል፣ ያነሳል፣

15) ለግብር ይግባኝ ጉባዔ የሚቀርቡ የግብር ወይም የታክስ አወሳሰን ጉዳዮችን ይከታተላል፣ ያስወስናል፣

16) ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 22. የትምህርት ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) የመማር ማስተማር ሥራን በበላይነት ይመራል፣

2) የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን፣ ኮሌጆችን፣ የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማትን፣ የትምህርት በሬዲዮ ማሠራጫ ጣቢያዎችን፣ አዳሪ ትምህርት ቤቶችን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣

**10)** Collect information necessary for tax assessment and consolidate thereon; determine and sue tax using the information;

**11)** Gather, Analyze and cause to proper functioning of information that serve for decisions and collection of untaxed city land possessions, house ownership, property and service payment;

**12)** Research on income decision and collection of city municipalities; collect and submit incomes to government treasury in accordance with the law;

**13)** Keep on the basis of the law, cause to keep and sell in auction the properties of tax or duty payers who failed to discharge their tax duties;

**14)** Investigate, decide, Impose and cancel penalties in accordance with the law on claims presented on tax and duty;

**15)** Follow up and cause for the decision of custom duty or tax appeal hearing body;

**16)** Perform other duties that can help to impleme desired objective.

## 22. Education Bureau

The Bureau shall have the following Power and Duties:-

1. Lead the learning and teaching works.
2. Establish and administer primary and secondary level schools, colleges, teacher training institutions, education through radio transmission stations and boarding schools.

3) የክልሉ ትምህርትና ሥልጠና ደረጃውንና ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣ መጽሐፍትንና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ያሟላል፣ ያሠራጫል፣

4) የመምህራን ድልድልና ምደባ ያካሂዳል፣ በየደረጃው ለማስተማር ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ ለመምህራን ስልጠና ይሰጣል፣

5) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና ያዘጋጃል፣ አፈፃፀሙን ያስተዳድራል፣ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

6) በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጁ ፈተናዎችን በክልሉ ያስፈጽማል፣

7) በክልሉ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናትና ወጣቶች የመማር ዕድል የሚያገኙበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

8) የአርብቶ አደር አካባቢ የትምህርት እንቅስቃሴ ያበረታታል፣ ልዩ ድጋፍ ይሰጣል፣

9) የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መማሪያ መጽሐፍት ህትመትና ስርጭት ያከናውናል፣

10) የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ትምህርት ቤቶችን የብቃት ደረጃ ያረጋግጣል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይሰርዛል፣

11) የትምህርት ተቋማትን የማስፈፀም አቅም ችግሮችን ይለያል፣ ዕቅድ በመንደፍ ለችግሮቹ መፍትሔ ይሰጣል፣

12) የመምህራንና የትምህርት አመራር አካላት የመፈፀም አቅም ይገነባል፣

13) የቅድመ መደበኛ፣ የልዩ ፍላጐት፣ የጐልማሶችና የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርቶችን አደረጃጀት ይወስናል ፣ መርሃ-ግብር ያወጣል፣ ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣

14) የመማር ማስተማር ምዘና አሰጣጥ ችግሮችና ውጤታማነት ላይ ጥናት ያካሂዳል፣ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ይቀይሳል፣ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣

3. Verity whether the region education and training activities are standardize and qualified, take the necessary measure, fulfill books and education aid materials and distribute there of;

4. Undertake allocation and assignment of teachers, verify the availability of conditions that make teaching capable in each level and provide training for teachers;

5. Prepare primary level education completion examination, administer the execution and grant certificate;

6. Execute nationally prepared examination in the region;

7. Devise strategy toward the access of learning to those children and youths whose age enough schooling in the region and implement same;

8. Encourage the educational activity of pastoral areas, and provide special support;

9. Undertake the publishing and distribution of primary and secondary level education learning text books;

10. Verify the standards of the state, non-governmental organization and private schools, grant license and cancel when necessary;

11. Identify the execution capacity problems of educations institutions and provide solutions to the problems through devising a plan;

12. Build the execution capacity of teachers and education leader's bodies;

13. Determine on the organization of pre-regular, special need, adult, and alternative basic educations, setting programs, follow up and supervise there of;

14. Conduct study on learning-teaching evaluation problems and effectivenesss, devise solutions and take the necessary measures;

15) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርትን ያዘጋጃል፣ በክልሉ ተግባራዊ ያደርጋል፣

16) ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## 23. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) በክልሉ የሚከናወኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች፣ አገር አቀፍ ደረጃቸውን ጠብቀው መካሄዳቸውን ያረጋግጣል፣

2) ደረጃውን የጠበቀ መሰረታዊ መለስተኛና መካከለኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ-ትምህርት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

3) በክልሉ የመሰረታዊ የመለስተኛና መካከለኛ ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ያቋቁማል፣ ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፣

4) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከክልሉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር መጣጣሙን ያረጋግጣል፣ ጥራትና አግባብነቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፣

5) ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆችና በዘርፉ ለሚሰማሩ ሌሎች ማሰልጠኛ ተቋማት የቅድመ-ዕውቅናና ዕውቅና ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል ከደረጃው በታች ሆነው ሲገኙ ፈቃዳቸውን ይሰርዛል፣

6) የትምህርትና ሥልጠና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ያዘጋጃል፣ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

7) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕከላት የቴክኖሎጂ የዕውቀትና ክህሎት ሽግግር ማዕከላት እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

15. Prepare primary level education curriculum, and implement in the region;

16. Implement other activities that enable to achieve the objective.

## 23. Technique and Vocational Education and Training Bureau

The Bureau shall have the following powers and duties:-

1. Verify whether the activities of technique and vocational education and training programs under taken in the region in line with the national standard;
2. Cause to prepare, follow-up and support standardized basic small and medium technical and vocational education and training curriculam;
3. Establish, expand, and administer basic, junior, and medium level technique and vocational education and training institution in the region;
4. Verify the compatibility of technique and vocational education and training with the region's demand of trained human power, follow up and supervise the quality and appropriateness thereof and take measures when necessary;
5. Grant pre-accreditation and accreditation license to those who engage in technique and vocational education and training colleges and other training institutions in the sector, renew their license and cancel when they finds below the standards;
6. Prepare procedure of professional competence assurance to education and training, follow up and supervise the implementation;
7. Support and follow up the technique and vocational education and training centers to be transformation center for technology, knowledge and skill;

8) ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የግል ባለሀብቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ያበረታታል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣

9) የክልሉን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ይፈፅማል፣ ያስፈጽማል፣

10) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ ምርምርና ሽግግር ተግባራትን በበላይነት ይመራል።

11) በቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚሰጡ ስልጠናዎች በተግባር ልምምድ እንዲደገፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

12) ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## 24. ጤና ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. በክልሉ ጤናና ጤና ነክ ጉዳዮችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣
2. የጤና አገልግሎት ሽፋን እንዲያድግ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፣
3. በብድርና ዕርዳታ የሚከናወኑ የጤና ፕሮግራሞችን አፈፃፀም ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣
4. የጤናውን ዘርፍ ልማት ክልላዊ ፕሮግራም ይነድፋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣
5. ክልላዊ የጤና መረጃ ሥርዓቱን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
6. ወረርሽኝና ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣
7. ክልላዊ የአመጋገብ ሥርዓት ስትራቴጂን አፈጻፀም ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣

8. Facilitate, encourage and offer the applicable support the conditions to private investors and non-governmental organization to engage in technique and vocational education and training sector;
9. Prepare technique and vocational education and training strategy, and implement and cause to implement upon permition;
10. Head the functions of research s and transfer of technology and extension services of industry;
11. Facilitate the conditions for training to offer in technical and vocational institution to be supported with actual practice;
12. Carry out other activities that enable to accomplish the objective.

## 24. Health Bureau

The Bureau shall have the following Powers and Duties.

1. Lead and coordinate health and health related affairs of the region;
2. Make the necessary Strive for the expansion of health service;
3. Follow up and coordinate the execution of health programs undertaken by loan and donation;
4. Design the health sector development regional program, follow up and evaluate the execution;
5. Lead and coordinate regional health data procedure, followupthe accomplishment;
6. Devise strategy that enables to prevent epidemic and communicable diseases, and follow up its execution;
7. Follow up regional dieting procedure strategy execution and coordinate there of;

ashamlaws.wordpress.com

8) የሕብረተሰቡን ጤና ሊጎዱ የሚችሉ ድንገተኛ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ የመከላከል እርምጃ ይወስዳል ያስተባብራል፣

9) በክልሉ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መድሐኒቶችና የሕክምና መሳሪያዎች በበቂ መጠን መኖራቸውንና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

10) በክልሉ የሚገኙ የመንግስት ጤና ተቋማትን ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣

11) የጤና ሥርዓቱን ካርታ ያዘጋጃል፣ የጤና መሰረተ-ልማቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ ድጋፍም ይሰጣል፣

12) በክልሉ ኤች አይ ቪ ኤድስን የመከላከል፣ የመቆጣጠርና የዘርፈ ብዙ ምላሽ ተግባርን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

13) የክልሉን የጤና ችግር ለመፍታትና የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የሚረዱ ምርምሮች እንዲካሄዱ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣

14) አግባብነት ያላቸው የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የጤና አጠባበቅ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣

15) በክልሉ የጤና ትምህርትና ስልጠና ተቋማትን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣

16) በክልሉ የምግብ፣ የመድሐኒትና ጤና እንክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፣

17) ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## 25. የሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

9) የሴቶችና ሕፃናት መብትና ጥቅሞችን በማስከበር ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፣

8. Take prevention measures and coordinate when an emergency conditions occurred that may endanger the health of the society;

9. Verify the presence of the necessary medicines and medical equipment at enough amounts and ensure their proper implementation;

10. Organize, and administer government owned hospitals that are found in the region;

11. Prepare the map of the health sector, undertake activities for medical infrastructure to be expanded and provide support there of;

12. Lead, coordinate, follow up and supervise the region's HIV/AIDS prevention, controlling activity and perform multi purpose responsive functions of the region;

13. Provide the necessary support to be conducted studies that may help to solve the health problem and improve the health service delivery of the region;

14. Make activities that health care education to be expanded by using the necessary different methods;

15. Establish, organize, and administer health education and training institutions in the region;

16. Verity the proper implementation of the administration and supervision of food, medicine and health care activities in the region;

17. Exercise other activity that help to accomplish the objective

## 25. Women and Children Affair Bureau

The Bureau shall have the following Powers and Duties

1. Undertake awareness and mobilization activities with regard to the protection of women and children rights and benefits;

2. ሴቶች በክልሉ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችላቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣

3. ሴቶች እንደየፍላጎቶቻቸውና እንደ ችግሮቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

4. በክልሉ መንግስት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፣

5. በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ መድሎዎችን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጥቃቶችን በጥናት በመለየት የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፣ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ይሰራል፣

6. በክልል ደረጃ የሴቶች የልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ስልት ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

7. ሴቶች በተለያዩ የመንግስት አካላት በውሳኔ ሰጪ የስራ ቦታዎች ላይ ለመመደብ በቂ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣

8. በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲመቻች ያደርጋል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፣

9. የሴቶች አደረጃጀቶችን አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ የስልጠና አገልግሎት የሚሰጥበትን አሰራር ያመቻቻል፣ ያስተባብራል፣

2. Ensure that opportunities which enable regional women to participate actively in economic and social activities have been facilitated;

3. Encourage and Facilitate women to struggle organizing in relation to their interest and problems, and resolve their problems;

4. Devise, evaluate and follow up the strategy to incorporate the affair of women and chilldren in policies, law, developmental programs and projects prepared by the regional state organs;

5. Identify through study discriminatory, harmful practices and abuse against women and children, and facilitate conditions to avoid the same, follow up its implementation and undertake awareness creation activity;

6. Devise a means to implement women's special help right at each level in the region, follow-up the implementation thereof;

7. Check whether proper concern has been given to women to assign on different decision making positions state organs;

8. Conduct studies that help to improve the life conditions of women who live at low standard of life, make to implement programs and projects through designing, facilitate accesses to credit and saving service and follow up the implementation there of;

9. Conduct studies, provide training, facilitate training opportunities and coordinate thereof to enable to foster the capacity of women and organizations;

ashamlaws.wordpress.com

10) የእናቶች የኑሮ ሁኔታ ስለሚሻሻልበትና የሕፃናት መብትና ደህንነት ስለሚጠበቅበት ሁኔታ ያጠናል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ ያደርጋል፣

11) ሴቶችንና ሕጻናትን የሚመለከቱ ሀገራችን የፈረመቻቸው አለም አቀፍ ውሎችና ስምምነቶች አፈጻፀም ይከታተላል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ሪፖርት ያቀርባል፡፡

12) ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 26. <u>የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) ወጣቶች በነፃ ፍላጎታቸው ተደራጅተው በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ በመልካም አስተዳደርና በልማት እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

2) የወጣቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች እንዲፈቱ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

3) የወጣቶችን ሁኔታ የሚያመላክቱ ዝርዝር መረጃዎችን ይሰበስባል ያደራጃል፣ይተነትናል በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ያደርጋል፣

4) የተደራጁ ወጣቶች ተገቢውን የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና የፋይናንስ ድጋፎች እንዲያገኙ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣

5) ወጣቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች የተለያዩ አካላት የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፤

6) በገጠር እና በከተማ በስራ አጥነት የተጋለጡ ወጣቶችን በአማራጭ የስራ መስኮች የሚሰማሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

10. Study on conditions for the improvement of mothers life condition and for the protection of children rights and safety and implement in cooperation with the concerning organs;

11. Follow up the implementation of international conventions and agreements concerning the regions women and children that Ethiopia is signed and report to the concerning organs thereof.

12. Perform other activities to achieve the objective.

## 26. Youths and Sport Bureau

The Bureau shall have the following power and duties

1. Make the necessary support to Youths to participate in integration on enhancement of democracy, good governance and development activities with their free will;
2. Create conduicive situation for youths in order to solve their economic, social and political problems;
3. Collect, organize and analyze detail information which depict condition of the youths; let the same to be know by concerned;
4. Make to organized youths to get the necessary to technical, material and financial support; follow-up its implementation;
5. Coordinate the activities that different bodies undertake concerning youths affair;
6. Facilitate the condition on which rural and urban youths who are unemployed to take part on alternative job fields;

7) ወጣቶችን በላቀ ደረጃ ተሣታፊና ተጠቃሚ የሚያደርጉ ጥናትና ምርምሮችን በማከናወን የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችንና ማዕቀፎችን ይቀርፃል፣ የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣

8) በክልሉ የመንግስት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የወጣቶች ጉዳይ እንዲካተቱ ስልት ይነድፋ፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤

9) የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላትን እንዲገነቡ ያስተባብራል ፣ ያስፋፋል፤

10) ወጣቶች በመልካም ስነ-ምግባር እንዲታነፁ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

11) የወጣቶች የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ተግባር በማሳደግ በጎነትን የክልሉ ባህል እንዲሆን ይሰራል፣ ያስተባብራል፣

12) የክልሉ ሕዝብን በስፖርት ለሁሉምና ባሕላዊ ስፖርት ተሣታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል፤

13) የሠለጠነ የሰው ኃይል ማፍራትና ብቃትን ለማሳደግ የስፖርት ትምህርት፣ ሥልጠናና ምርምር ተቋሞች የሚቋቋሙበትን ሥልት በመቀየስ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

14) የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችንና የስፖርት ማበልፀጊያ ማዕከላትን ያስፋፋል፤

15) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ህክምና አገልግሎት ያደራጃል፤ በስፖርት አበረታች መድኃኒቶችና ዕፆች መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

16) የክልሉን የስፖርት ማኀበራትን ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡

17) የስፖርት ውድድሮችን እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፣

18) ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

7. Draft strategies and frome works through implementing study and researches which make youths highly participant and beneficiary; put working procedures;

8. Draft, evaluate and make the necessary support a means to include youths affair in policies, laws, development plogram end projects which to be prepared by government body in the region;

9. Coordinate and expand to build centers of building youths personality;

10. Facilitate the conditions by which youths to be equipped with better ethics;

11. Work and coordinate to make goodwill to be culture of the region by enhancing good will service of the youths;

12. Make all regional people to participant and beneficiary on sport for all and cultural sport;

13. Devise asystem for the building of sport education, training and research institutions to rise-up the efficence and produce trained human power; make to accomplish the same;

14. Expand sport exercising centers and sport fields;

15. Organize sport medical service in collaboration with the concerned organ; lay-down aprocedure that enable to prevent the use of doping and medicine in sport;

16. Register and offer the necessary support sport association of the region;

17. Make and coordinate sport competitions to be organized;

18. Accomplish other activities to implement the objective.

## 27. የባህልና ቱሪዝም ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩል፣

1) የክልሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋ፣ ባህል፣ ቅርስና ኪነጥበብ እንዲጠበቁ፣ እንዲጠኑና እንዲታወቁ ያደርጋል፣

2) የክልሉ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች፣ የፊልምና የትያትር ዘርፎች እንዲለሙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፣

3) የባህልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች፣ ድርጅቶችና ማህበራት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል በሕግ መሰረት ይሰርዛል፣

4) ማህበራዊ ዕድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን እና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ያከናውናል፣

5) በክልሉ የሚገኙ ቁሳዊና ቁሳዊ ያልሆኑ የባህል ቅርሶችን ያሰባስባል፣ ይመዘግባል፣ እንዲጠበቁ ያደርጋል፣

6) በክልሉ ተፈጥሮአዊ የቱሪዝም መስዕቦችና የዱር እንስሳት መገኛ ቦታዎችን ያጠናል፣ አዋጭነታቸውን አረጋግጦ እንዲከለሉና እንዲጠበቁ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣

7) የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲስፋፉና የአካባቢው ሕዝብ ከቱሪዝም ልማት ተጠቃሚ የሚሆንበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፣

8) የክልሉን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባህል፣ ቋንቋ ታሪክና ቅርስ የሚያሳይ ቤተ-መዘክርና ባህላዊ መንደሮች ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣

9) በክልሉ የሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ክልሎችና ሌሎች የቱሪስት መስሕብ ስፍራዎች የሚገኙ ገቢዎችን ይሰበስባል፣

## 27. Culture and Tourism Bureau

The Bureau shall have the following powers and duties

1. Undertake activities that the language, culture, heritages and arts of the Nations, Nationalities and Peoples of the Region to be conserved, studied and known;
2. Undertake activities the Nations, Nationalities and Peoples historical and cultural heritages, film and theatre sector to be developed and conserved in the Region;
3. Grant professional competence license to investors, organizations and associations engaged in the sector to expand the tourism industry, supervise and cancel the same in accordance with the law;
4. Perform awareness creation activities that enable to prevent attitudes and harmful customary practices that hinder social development;
5. Collect, register and make to be conserved material and non materials traditional heritages that are found in the region;
6. Study natural tourist attractions and wild life areas, and demarcate and conserve after verifying their feasibility and supervise there of;
7. Devise strategy to expand tourism service delivering organization and means of benefiting the surrounding people from the tourism development and implement there of;
8. Organize and administer museums and cultural village showing the culture, language, history and heritages of the Nation, Nationalities and peoples of the region;
9. Collect revenues from wildlife conservation areas and other tourist attraction areas administered by the region;

ashamlaws.wordpress.com

10) በክልሉ ለሚገኙ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ክልላዊ ደረጃ ይሰጣል፣

11) በሰው ሃይል ሥልጠናና በሙያ ምክር አገልግሎት አማካይነት የቱሪዝም ዘርፍን የማስፈፀም አቅም ይገነባል፣

12) ለቱሪዝም ገበያ አስፈላጊ ሆነው የሚገኙ የዱር እንስሳት እርባታ ጣቢያዎችን እና ፓርኮችን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል።

13) ፓርኮች እንዲጠበቁ ያደርጋል፤ ልማትና አስተዳደራዊ ስራዎቻቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

14) ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## 28. ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማትና ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) የክልሉ መንግስት ሲቪል ሰርቪስ ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን ያረጋግጣል፣

2) የክልል መንግስት ሰራተኞች ምልመላና መረጣ በብቃት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያደርጋል፣

3) የሲቪል ሰርቪሱ የሰው ኃይል በቀጣይነት በሚለማበትና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣

4) ለሲቪል ሰረቫንቱ በብቃትና በአፈጻፀም ውጤታማነት ላይ የተመሰረተ የክፍያና የማበረታቻ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ይገመግማል አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃ ይወስዳል፣

5) የክልሉ የመንግስት ሰራተኞች ሥነ-ምግባር መከታተያ ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፣

6) የክልሉ መንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ሕጎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

10. Grant regional standard to tourist service delivering institutions that are found in the region;
11. Build the execution capacity of the tourism sector by means of man power training and expertise consultancy service;
12. Establish and administer wild life rearing stations and ranches that finds to be necessary to the tourism market;
13. Make the parks to be protected, fullow-up and support development and adminstirative activities;
14. Perform other activities to implement the objective.

## 28. Public Service and Human Resource Development Bureau

The Bureau shall have the following powers and duties.

1. Verify whether civil service of the regional government has the efficiency and its being effectiveness;
2. Undertake activities to make the recruitment and selection of civil servant to be performance based;
3. Devise strategy for sustainably development and utilization of the civil service human power and follow up the implementation;
4. Establish procedures of payment and encouragement to the civil servants on the basis of performance and effective execution, evaluate the effectiveness and take the necessary improvement measures;
5. Cause that a procedure to be laid down for the ethics liasion of the regional state employee and follow up the implementation;
6. Follow up and verify the proper implementation of the employee administration laws of the regional state;

7) የመንግስት ዘርፍ አቅም ግንባታ ስራዎችን ያስተባብራል፣ የመንግስት ዘርፍ አገልግሎት በቀጣይነት የሚሻሻልበትና ውጤታማ የሚሆንበትን ስልት ይቀይሳል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይገመግማል፣

8) የክልል መንግስት መስሪያ ቤቶችን አደረጃጀት አግባብነትን ይመረምራል፣ በአደረጃጀት ማሻሻያ ጥናቶች ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣

9) በክልል መንግስት መስሪያ ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ፣ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፣

10) የሲቪል ሰርቪሱ የሰው ሃብት አመራርና የተቋማዊ መረጃዎች ሥርዓት በወጥነት እንዲዳብርና እንዲተገበር ያደርጋል ማዕከላዊ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፣

11) የመንግስት ሰራተኞች የሚያቀርቡትን አቤቱታዎችና ይግባኞችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣ ያልተፈፀሙ የሲቪል ሰርቪስ ቅሬታና ይግባኝ መወሰኛ ስራ ሂደት ውሳኔዎችን ለአፈፃፀም ወደ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ያስተላልፋል፣

12) የክልሉን የመንግስት መስሪያ ቤቶችን የሰው ሀብት አስተዳደር በበላይነት ይመራል፣ የስራ አመራር መመሪያዎችና የአፈፃፀም መስፈርቶችን ያዘጋጃል ያስፈፅማል፣

13) የመንግስት ሰራተኞችን የደመወዝ፣ የልዩ ልዩ አበሎችና ጥቅማ ጥቅሞች ማሻሻያ ያጠናል ሲፈቀድም ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

14) በሕግ መሰረት የክልሉ መንግስት ሰራተኞችን ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ በአገልግሎት ላይ ስለማቆየት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣

15) የክልሉ ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣

16) ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

7. Coordinate the capacity building activities of the regional state sector, devise strategy for the sustainable improvement and effectiveness of the service of the regional state sector and follow up and evaluate the implementation;

8. Investigate the appropriateness of the organization of the regional state offices, provide the necessary support to studies regarding organizational improvement;

9. Verify service delivery standards, and the establishment and implementation of claim submission and settlement procedure in the regional state offices;

10. Undertake activities consistently to develop and implement the human resource management and institutional information procedure of the civil service, and serve as source of information center;

11. Decide on appeal and claims of government employees, transfer the civil service unimplemented claims and appeal deciding work process decisions to ordinary courts for implementation;

12. Head the administration of human resource of the state offices, prepare management guideline and implementing requirements and cause to implement same;

13. Study the improvement of salary, allowance, and different benefits of state employee, and implement upon permission;

14. Decide on requests about the extension of the service of the state employee above the age of retirement pursuant with the law;

15. Head, follow up and coordinate the functions of information communication technology of the region;

16. Carry out other activities to achieve the objective.

## 29. የፍትህ ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሕግ ጉዳዮችን በሚመለከት የክልሉ መንግስት አማካሪ ሆኖ ይሰራል፣

2) በፌዴራልና በክልሉ ሕገ-መንግስታት እና በሌሎች ሕጎች የተደነገጉ የግልና የቡድን መሰረታዊ ነፃነቶችና ሰብዓዊ መብቶች መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ ከሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች ጥሰት ጋር የተያያዙ አቤቱታዎችን ምርመራ ይመራል፣ አስተያየት ይሰጣል፣ የመፍትሔ እርምጃዎችን ይወስዳል፣

3) በክልሉ መንግስት ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ወንጀል ተፈፅሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ ከፖሊስ ጋር በጋራ ያካሂዳልወይምእንዲካሄድ ያደርጋል፣ የምርመራሂደቱን በበላይነት ይመራል፣ይቆጣጠራል፣ የጥፋተኝነት ድርድር ይፈቅዳል፤ ክስ ይመሰርታል ወይም እንዲመሠረት ያደርጋል፣ ይከራከራል፣ በቂ ምክንያት ሲኖር በህግ መሰረት የተጀመረ ምርመራ እንዲቋረጥ ወይም ክስ እንዲነሳ ያደርጋል፣ ፍርድ ቤቶች የሚሠጡዋቸውን ውሳኔዎች ይከታተለል፤

4) የወንጀል ድርጊት ጠቋሚዎችና ምስክሮች በህግ መሰረት ጥበቃና ከለላ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

5) በወንጀል ድርጊት ወይም በሰብዓዊ መብት መጣስ ምክንያት ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው በክልሉ ፍርድ ቤቶች ክስ ለመመስረትና ለመከራከር አቅም የሌላቸው ዜጎችን ያማክራል፣ እንደአስፈላጊነቱ ወክሎ ካሳ እንዲያገኙ የፍትሐብሔር ክስ ይመሰርታል፣ በተለይም በሴቶችና ሕፃናት ላይ ለሚፈፀሙ ጥቃቶችና ወንጀሎች ልዩ ትኩረት ይሰጣል፣

6) በግል አቤቱታ የሚያስቀጡና ቀላል ወንጀሎች በዕርቅ የሚጠናቀቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

## 29. Justice Bureau

**The Bureau shall have the following Powers and Duties**

1. Work as higher advisor for the regional government concerning legal affairs;
2. Ensure the protection of individual and groups fundamental freedoms and human rights enshrined under the federal and the regional constitutions and other laws, investigate claims in relation to violation of human rights and freedoms, provide remarks and take measures of remedial;
3. Investigate and cause to investigate jointly with police when believed that crime committed under the jurisdiction of the courts of the regional government, head and supervise investigation process, permit culpable litigation, open and cause to open charge, litigate, order the discontinuance or withdrawal of an investigation commenced in accordance with the law where sufficient grounds are there and follow-up the decisions made by courts;
4. Enable whistleblowers and witnesses of criminal acts to get protection and shelter pursuant with the law;
5. Advice citizens who are vulnerable due to criminal acts or human right violation, and who does not have the capacity to sue and litigate in the region's court. As necessary represent and instituted civil case to be compensated, especially acts and crimes committed against children and women shall be given special concern;
6. Facilitate conditions to settle crimes of individual claims and petty offences through reconciliation;

7) በወንጀል ድርጊት ተጠርጥረው የተያዙ ወይም የታሰሩ ወይም በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች አስተዳደርና አያያዝ በሕግ መሰረት መሆኑን ይቆጣጠራል፣ ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣

8) የክልሉን ህዝብና መንግስት መብትና ጥቅም ለማስከበር በማናቸውም የፍትሐብሔር ጉዳዮች የክልሉን መንግስት መስሪያ ቤቶችን እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን እና የህብረት ስራ ማህበራትን በመወከል ሥልጣኑ በሚፈቅድለት ፍርድ ቤት ወይም በማንኛውም ዳኝነት ሰሚ አካል ክስ ይመሰረታል፣ ይከራከራል ወይም በማናቸውም የክርክር ደረጃ ጣልቃ ገብቶ ይከራከራል፣

9) የክልሉን መንግስት መስሪያ ቤቶችን ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ስምምነት የሚያደርጉባቸውን ውሎችን፣ የመግባቢያ ሰነዶችን እና ሌሎች የስምምነት ረቂቅ ሰነዶችን ያዘጋጃል፣ ይከታተላል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

10) በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች እና በግል ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች መካከል የሚከሰቱ የፍትሐብሔር ክርክሮች በድርድር እንዲያልቁ ጥረት ያደርጋል፤ ድርድሩ ካልተሳካ ጉዳዩን ስልጣኑ ለሚፈቅድለት ፍርድ ቤት አቅርቦ ይከራከራል፣

11) የክልሉን መንግስት ሕግ ያዘጋጃል፣ አስተያየት ይሰጣል፣

12) የክልሉን ሕጎች ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ያጠቃልላል፣ በባለአደራነት ይይዛል፣ ያሰራጫል፣ የግንዛቤ መፍጠር ስራ ይሰራል፣

13) የክልሉንና የፌዴራል መንግስታት ሕጎችን የማጣጣም ስራ ይሰራል የሕግ ማሻሻያ ሀሳቦችን ያመነጫል፣

14) በክልሉ ፍርድ ቤቶች ለሚከራከሩ ጠበቆች ፈቃድ ይሰጣል ያድሳል፣ ይሰርዛል፣ ስራቸውን ይቆጣጠራል፣ የጠበቆችን ዲሲፕሊን ጉዳዮች አይቶ ይወስናል፣

7. Supervise whether the administration and keeping of a person accused, or arrested, or held in custody and convicted prisoners are in accordance with the law and take appropriate lawful measure;

8. Sue, litigate or intervene in any proceedings of civil cases in pertinent courts or in any other judicial organ by representing the state offices and, if necessary, government development enterprises and cooperative associations to protect the rights and benefits of the people and the regional state;

9. Prepare, follow-up and support contracts, memorandum understanding and other agreement documents by which the regional state offices make an agreement with third parts;

10. Strive civil cases to be settled by negotiation raised between the state offices and private organization or individuals; litigate in pertinent court when the negotiation fails to resettle the case;

11. Prepare legal draft of the regional state and provide remarks thereof.

12. Collect, organize, consolidate, keep as trustee, and distribute laws of the region and undertake awareness creation activity;

13. Undertake compatibility activity of the regional and federal laws, Initiate amendment ideas of law;

14. Grant, renew, cancel license to attorneys who litigate in the courts of the region, supervise their activity and decide on attorneys disciplinary cases;

ashamlaws.wordpress.com

15) በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የኢትዮጵያውያን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ይመዘግባል፣ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ በሕግ መሰረት ይሰርዛል፣ ስራቸውን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፣

16) አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሰነዶችን ይመዘግባል፣ ያረጋግጣል፣ ይሰርዛል፣ ይሽራል፣

17) ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 30. ፀጥታና አስተዳደር ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. የክልሉን የፀጥታ ሁኔታ በሚመለከት ጥናትና ክትትል ያደርጋል፣ የፀጥታ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል የክልሉን ሰላም ያረጋግጣል፣
2. የክልሉን ሕዝብ ደህንነት፣ ሰላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር ተባብሮ ይሠራል፣
3. በክልሉ ውስጥ ዘመናዊ የሆነ የፀጥታ መረጃ ፍሰት አያያዝና አደረጃጀት እንዲኖር ስልት ይቀይሳል፣ ይተገብራል፣
4. የፀጥታ መረጃ ለማሰባሰብና ለማስተዳደር የሚረዳ ልዩ የፋይናንስና የበጀት አስተዳደር እንዲሁም የሰው ኃይል አስተዳደር ደንብ በመስተዳድር ምክር ቤት ውሳኔ ተግባራዊ ያደርጋል፣
5. ከአጎራባች ክልሎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ፀጥታን በሚመለከት ግንኙነት ያደርጋል፣ በድንበር አካባቢ ያለውን ህብረተሰብ ግንኙነት እንዲሻሻልና እንዲጠናከር የሚረዱ ሥራዎችን ይሠራል፣

15. Register charity organizations and associations working in the region, grant certificate of legal personality, cancel in accordance with the law, supervise and verify their activity;

16. Record, check, cancel and repeal documents pursuant to relevant law;

17. Perform other activities to achieve the objective.

## 30. Security and Administration Bureau

The Bureau shall have the following Powers and Duties

1. Study and follow up conditions concerning the security of the region, collect, evaluate, distribute and functionalize information and there by maintain the region's peace;
2. Work in cooperation with proper organs to ensure the safety, peace, and security of the people of the region;
3. Devise and implement strategy to have modern security information flow, keeping and organization in the region;
4. Put in to practice, upon the decision of administrative council, administration of special finance and budget in order to collect and administer security data as well as human power administration;
5. Make relations with neighboring regions and concerning bodies regarding security, undertake activities that help to improve and reinforce the relation of the community who live in border areas;

6. ክልሉ በሚያዋስናቸው ጐረቤት አገሮች ድንበር አካባቢ የግጭት ሁኔታ በመከታተል መረጃ ያሰባስባል፣ ግጭት እንዳይከሰት የመከላከል ሥራዎችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ይሠራል፡፡ሲከሰትም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

7. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በግጭት መነሻ ምክንያቶች ላይ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ የመፍትሔ ሃሳቦችና የአፈፃፀም ስትራቴጂዎችን ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

8. በክልሉ በሚገኙ የአስተዳደር እርከኖች መካከል ግጭቶች እንዳይነሱ የመከላከል ሥራዎችን ይሠራል፣ ሲከሰቱም በቁጥጥር ሥር ያውላል፣ የግጭቱን መንስዔ አጣርቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣

9. በተለያዩ ሃይማኖትና እምነት ተከታዮች መካከል ሠላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግና ግጭትንም ለመከላከል እንዲቻል አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት፣ የሃይማኖት ተቋማትና ከሌሎች ማናቸውም አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

10. በክልሉ ውስጥ በሚንቀሣቀሱ የሀይማኖትና እምነት ተቋማት ተከታዮች መካከል ሠላምና መከባበርን በማጎልበት ግጭትና አለመግባባትን ለመከላከል እንዲቻል አግባብነት ካላቸዉ አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤ የኃይማኖትና የእምነት ተቋማትን ይመዘግባል፤ ፈቃዳቸዉን ያድሳል፤ ከህግ ዉጭ ሆነው ሲገኙ አግባብነት ካላቸዉ አካላት ጋር በመነጋገር ይሰርዛል፤

11. የፀረ-ሰላም ኃይሎችን እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ በዚህም የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ አሠራሮችን አጥንቶ ተግባራዊ ያደርጋል፣

12. በክልሉ ውስጥ ባሉ አስተዳደር እርከኖች መካከል የሚነሱ የማካለል ጥያቄዎች በሠላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ያደርጋል፣

13. የክልሉን የፖሊስና ማረሚያ ፖሊስ ኮሚሽኖችን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣

6. Collect information through following up the conflict circumistances in areas bordering the region with neighboring countries; undertake conflict protection activities collaboration with the concerning body and resolve the same in coordination with concerning bodies when it is raised;

7. Conduct study and research on causing factors of conflict in cooperation with concerning bodies, put forward solutions and execution strategy and implement when it is permitted;

8. Undertake protection activity not to raise conflict among the administrative levels of the region, under-control when they arise and submit the cause of the conflict to the concerned body;

9. Work in collaboration with relevant government bodies, religious institutions and any other bodies to settle peace and respect ,and prevent confilict among different religions and faith followers;

10. Undertake activities in collaboration with appropriate bodies to capable the prevention of confilict and misunderstanding in order to enhance peace and respect among religion and faith followers who exercise in the region, register religion and faith institutions, renew their license, cancel when found illegal by dealing with relevant bodies;

11. Follow up the movement of anti- peace forces, conduct study and implement methods that enable to solve the problems in this regard;

12. Resolve peacefully the questions of demarcation arousing among the administrative levels of the region;

13. Head,follow-up and coordinate the functions of police and prison police commissions of the region;

14. በክልሉ በተለያዩ የአስተዳደር እርከኖች ከብሔረሰቦች ማንነት ጋር ተያይዘው በሚነሱ የድንበር ማካለል ጉዳዮች በብሔረሰቦች ምክር ቤት የሚሰጡትን ውሣኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል ፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
15. የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በአስቸኳይ በቁጥጥር ስር ለማዋል እንዲቻል ሲታዘዝ የፀጥታ ኃይል ያሠማራል፣
16. የፀጥታ መደፍረስ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት በሚወሰደው የመከላከል እርምጃ በሴቶችና በህፃናት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የጥንቃቄ እርምጃ ይወስዳል፣
17. የሚሊሽያ ኃይልን አቅም በመገንባት የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ እንዲጠበቅ ያደርጋል፣
18. ሚሊሻውን ፀጥታን ለማስከበር በሚያስችል አኳኋን ያደራጃል፣ እንደአስፈላጊነቱ ከህዝቡና ከሌሎች የፀጥታ ኃይሎች ጋር በቅንጅት የሚሰራበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
19. ሚሊሺያው ለረጅም ጊዜ ከምርት ሥራው ሳይነጠል በፀጥታና ሌሎች መንግሥታዊ ሥራዎች ላይ እንዲሰማራ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
20. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

31. **የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) የክልሉ መንግሥት ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ስራን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤የኮሙኒኬሽን ሥራ አገልግሎት ይሰጣል፣ ሥርዓት ይዘረጋል፣
2) የክልሉን መንግሥት ሴክተር መሥሪያ ቤቶች የህዝብ ግንኙነት ሥራ ያስተባብራል ይከታተላል።
3) የክልሉ መንግሥት ቃል አቀባይና የኢንፎርሜሽን ዋነኛ ምንጭ በመሆን ያገለግላል፣ በልዩ ልዮ መንገዶች ያሰራጫል፣ በሀገራዊና በክልላዊ ጉዳዩች ላይ የክልሉን መንግስት አቋም ይገልጻል፣

14. Functionalize the decisions that the nationalities council passes on boundary demarcation issues which arises among various administrative levels of the region with regard to ethnic identity and follow up the implementation there of;
15. Deploy security force upon order to enable the under-control of natural and man made disasters;
16. Take cautionary measure to avoid dangers against women and children when protection measures taken toward security violation and natural disaster;
17. Make to be maintained the peace and security of the society through building the capacity of the militia force;
18. Organize the militia in away that enable to maintain security and, as necessary, facilitate conditions to work in cooperation with the public and other security forces.
19. Follow up and supervise the militia in order to deploy on security and other state activities without departing them from production activity for a long time;
20. Perform other activities to achieve the objective

31. **Office of Government Communication Affairs**

The office shall have the following power and duties:-

1. Head and coordinate information and communication activities of the regional government, offer services of communication activities, and lay down system;
2. Coordinate and follow- up public relation activities in sector bureaus of the regional government;
3. Serve as spokes person and main source of information to the regional government, disseminate the same by various mechanisms and disclose the stand of the regional government on national and continental matters;

4) የክልሉን መልካም ገጽታ የሚያጎለብት ሁነቶችን ይፈጥራል፣ ያስተባብራል፣ ያስተዋውቃል፣ በነዚሁ ተግባራት ላይ የሚያተኩሩ የሚዲያ ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁ እና እንዲሰራጩ ያደርጋል፤

5) የክልሉን፣ የሀገር አቀፍና የውጭ ሚድያ የዕለት ተዕለት ዘገባዎችን በመቃኘት ሥራዎችን ያከናውናል፣ ትንተና ያዘጋጃል እንዲሁም የሕዝብ አስተያየት በማሰባበሰብ እና በመተንተን ያሠራጫል፣

6) በክልሉ ሚዲያ በዓይነትም ሆነ በብዛት የሚስፋፉበትንና ስርጭቱ እየሰፋ የሚሄድበትን እንዲሁም ልዩ ድጋፍ የሚሹ አካባቢ ህዝቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ከመንግስት መረጃ እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

7) የማስታወቂያ ሥራ ሕግን ተከትሎና ለሃገር እና ለክልሉ ልማት አስተዋፅኦ ሊያደርግ በሚችልበት አቅጣጫ ስለመከናወኑ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

8) ልዩ ልዩ የሕትመትና የኦዶዮቪዥዋል ሥራዎችን ይሠራል፣ የአርማና የህትመት ዲዛይን ሥራዎችን አገልግሎት ይሠጣል፣

9) ስርጭታቸው በክልሉ ለተወሰኑና በየጊዜው የሚወጡ የንግድ ፕሬሶች ይመዘግባል፣ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ እንዲሁም የንግድ ዓላማ ለሌላቸው ፕሬሶች ፈቃድ ይሰጣል፣ በሕግ መሰረት መስራታቸውን ያረጋግጣል፣

10) ለሚሰጠው አገልግሎት በሕግ መሠረት ክፍያ ይሰበስባል፣

11) ዓላማውን ለመፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**32. የአካባቢ ጥበቃና ደን ባለሥልጣን**

ባለሰልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1) በመንግሥትም ሆነ በግል ፕሮጀክቶች፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ የልማት ህጎችና መርሃ ግብሮች ላይ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣

4. Create, coordinate and disclose the circumstances that enhance the good image of the region; cause to prepare and disseminate media programs that focus on thereof;

5. Undertake activities by searching for the daily news of regional, national and foreign Medias, prepare analysis as well as disseminate public views through collecting and analyzing;

6. Facilitate conditions by which the media expands and breaks through in kind and in number as well as to make those people and environment that needs special support to be equal beneficiary in the region;

7. Make follow-up and supervise that the functions have been carrying out following advertising law and in a way that capable to make contribution to the development of the region;

8. Follow up and Perform different print and audiovisual activities and render service on logo and print design;

9. Register and certify competence assurance to trade presses and to those which their distribution is limited in the region as well as grant license to those presses which do not have trade objective and ensure that they are being working based on the law;

10. Collect payment legally for the service it renders;

11. Perform other duties to achieve its objective.

**32. Environmental Protection and Forest Authority**

The Authority shall have the following powers and duties:-

1) Lay-down a system that enable to Carry out evaluation of environmental impact on social and economical development laws and programs, government and private projects;

ashamlaws.wordpress.com

2) ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት ፓሊሲዎችን ለማስፈፀም አሰፈላጊ ሕጎች ከመውጣታቸው በፊት በአከባቢ ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ በመገምገም የውሣኔ ሃሣብ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣

3) በክልሉ የስልጣን ወሰን በሚካሄዱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮጀክቶች በአካባቢ ላይ የሚኖራቸው ጉልህ ተጽዕኖ እንዲገመገም ያደርጋል፣ የአካባቢ ተጽዕኖ ጥናት ዘገባ ሲቀርብለት ይገመግማል፣ ለፈቃድ ሰጪው አካል ውሣኔውን ያሳውቃል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፣

4) በክልሉ ሥልጣን ወሰን ውስጥ ማናቸውም የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ ድርጅቶችና ተቋማት አካባቢን ከብክለትና የደን ጥበቃ ግዴታዎች ለማስጠበቅ የወጣውን ህግ ጠበቀው መንቀሳቀሳቸውን በማናቸውም መሬት ወይም ቅጥር ግቢ በመግባት ያረጋግጣል፣ ናሙና ይወስዳል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣

5) በሀገሪቱ ህግ መሠረት የወጡ የአካባቢ ደረጃዎች በሥራ ላይ መዋላቸዉን ያረጋግጣል

6) ጽዱና አረንጓዴ አካባቢን ለመፍጠር የደረቅና የፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤ ቆሻሻን መለሶ ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ አማራጮችን እና ምንጮችን ይለያል፤ ተግባራዊ እንዲሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሠራል፣

2) Present decision proposal to concerned body by assessing the impact of social and economic development policies before issuing laws to implement thereof;

3) Cause to evaluate the impact that social and economic development projects, which being carried on within the scope of authority 0f the region, have on environment, evaluate upon submission impact study report of the environment, disclose its decision to the body which grant license, follow-up and supervise the implementation, take the necessary measure;

4) Ensure by getting inside the fence and land that any production or service organizations or institutions have been working by keeping the law which issued to keep environmental contamination and obligation of foresters protection with the scope of the region authonty, take sample, control the same; take the legal measure if found necessary;

5. Ensure whether that environmental standards issued based on the country's law have been put into practice;
6. Cause to lay-dawn a system for handling and disposal of dry and wet wastes in order to create neat and green environment; identify technology options and sources that enable to re-use the dissipate, work in integration with the concerned organ to implement the same;

7) አደገኛ ነገሮችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ማዘዋወርን፣ አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ የወጡ ፖሊሲዎችና ሕጎችን ተፈፃሚነታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣

8) በአካባቢ ሀብቶች አጠቃቀም ዘላቂ የአካባቢ አያያዝ ለማስፈን የአካባቢ አመላካቾች መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፣ የተቀናጀ የአካባቢ ሁኔታና ለውጥ ዘገባ ያዘጋጃል፣ በጥናቱ መሠረት እንዲተገበር ያደርጋል፣

9) በረሃማነትን ለመከላከልና የተራቆቱ አካባቢዎች ሥነ-ምህዳር መለሶ ማገገም እንዲችል ስልቶችን ይቀይሣል፤ አግባብ ባላቸው አካላት መተግበሩን ይከታተላል፣

10) የክለሉን ብዝሃ ህይወት ሃብት አያያዝና አጠቃቀም በተመለከተ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ ስልቶችን ይቀይሣል፤ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ ተግባራዊ ያደረጋል፣

11) የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያለማል እንዲለማ ያደርጋል፣ ከማናቸውም ጉዳት እንዲጠበቅ ያደረጋል፤ የምርት ሰጪ ደኖች አጠቃቀም ይወስናል፣ የምክርና የሥልጠና አገልግሎት ይሰጣል፣

12) የደን ምርምርና ልማት ለማስፋፋት የሚያስችሉ የምርምር፣ የግብዓት ማባዣ፣ የደን ዕፅዋት ዘር ጥራት ቁጥጥር ማዕከላትና ላቦራቶሪወችን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣

13) ለደን ልማት፣ ለደን ውጤቶች አጠቃቀምና ዝውወውር ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ በህግ አግባብ እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፣

7. Follow-up and supervise the implementation of policies and laws which issued regarding usage, handling, transfer, and production of dangerous things and by products;
8. Lay-down a system of collection, organization and usage of information of environment indicators in order to settle sustainable environmental keeping in environmental resources usage; prepare integrated report about the condition and change of the environment; make to be implemented the same based on the research;
9. Devise a system to recover the ecology of bared environment and to prevent desertification, follow-up the implementation by the appropriate body;
10. Conduct research, devise means, lay-down procedure, create awareness and implement handling of bio-diversity resource and usage of the region;
11. Lay-down a system of development and usage and protection of natural and man made forest; develop and cause to develop the same, make to be protected from any catastrophy; decide the usage of productive forest; give consultation and training service;
12. Establish and administer research, input multiplication, forest seed quality control center and laboratory to enlarge research and development of forest;
13. Grant and supervise license for forest development, transfer and usage of forest produc; take and cause to take measure with relevant law;

14) ከብሔራዊና ክልላዊ ፓርክ ውጪ ያሉ የዱር እንስሳት ሀብት ይጠብቃል፣ ሕገ ወጥ የዱር እንስሳት አደን ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድም ያደርጋል፣ ስለዱር እንስሳት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል፣

15) ጥብቅ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ደኖች የሚሰጡትን የሥነ-ምህዳር አገልግሎት በገንዘብ እንዲተመን በማድረግ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ከሚመለከተው ጋር በመቀናጀት የደን ካርቦን ሽያጭ እንቨስትመንት እቅድ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ይሠራል፣

16) ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል አምስት
## የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች መዋቅር እና ኃላፊዎች

### 33. የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች በየደረጃው የሚቋቋሙ ስለመሆኑ

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋሙ አስፈጻሚ አካላት መሥሪያቤቶች እንደሁኔታው በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ፣ በከተማና በክፍለ ከተማ ደረጃ ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ በመስተዳድር ም/ቤቱ ይወሰናል፡፡

2) የአስተዳደር ምክር ቤት አባል የሆኑ በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ የአስፈፃሚ አካላት መስሪያ ቤቶች ተጠሪነት ለዋና አስተዳዳሪውና ለአስተዳደር ምክር ቤቱ እንዲሁም በየደረጃው ላሉ የአስፈፃሚ አካላት መስሪያ ቤቶች ይሆናል፡፡

3) ለአስፈፃሚ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በየአስተዳደር እርከን ላሉት መስሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

14. Protect wild animal resource which are outside National and regional park, control illegal wild animal hunting, take and cause to take measure, work in integration with the concerned body about wild animals;

15. Prepare investment plan of forest carbon sale in coordination with concerning body to ensure utilization through making the ecological service, which protected natural and man-made forests offer, to be priced interms of money, work out to implement the same;

16. Carry out other functions to achieve the objective.

## PART FIVE
## STRUCTURE AND HEADS OF OFFICES OF EXECUTIVE ORGANS

### 33. Establishment Of Offices Of Executive Organs at Various Levels:-

1. Offices of executive organs established in accordance with article (3) of this proclamation may be established at the level of Zone, Special woreda, Woreda, City, Sub-city; details shall be decided by Administrative Council;
2. Executive institutions at different levels and member of administrative council are accountable to their head administrator and administrative council as well as the executive organs at each level;
3. Power and duty given to government executive institutions may be, as may be necessary, implemented on institutions at administration hierarchy;

4) እያንዳንዱ የአስፈፃሚ አካላት መስሪያ ቤቶች ኃላፊና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ኃላፊዎች፤ እንዲሁም የሥራ ሂደት ባለቤቶች እና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

5) ተቀራራቢ ተግባር ያላቸው የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች አንድ የድጋፍ ሰጪ ማዕከል በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

6) በየደረጃው ያሉ አስፈጻሚ መሥሪያቤቶች በየአስተዳደር ዕርከኑ እንደ-አስፈላጊነቱ ተቀናጅተው ወይም ተጣምረው ሊደራጁ ይችላሉ፡፡

## 34. የአስፈፃሚ አካላት መስሪያ ቤት ኃላፊዎች ተጠሪነት፣ ሥልጣንና ተግባር

1) የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት የሆኑ የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች ለርዕሰ መስተዳድሩ እና ለመስተዳድሩ ምክር ቤት ተጠሪ ይሆናሉ፡፡

2) እያንዳንዱ የአስፈፃሚ መሥሪያ ቤት ኃላፊ፡-

ሀ/ ለመሥሪያ ቤቱ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣

ለ/ መሥሪያ ቤቱን ይወክላል፤ ያስተዳድራል፣

ሐ/ ሥራንና ሠራተኛን ይመራል፣

መ/ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፣ አፈፃፀሙንም ለመስተዳድር ምክር ቤት ሪፖርት ያደርጋል፣

ሠ/ በሕግ ለመሥሪያ ቤቱ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

3) የዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች እንደ አግባብነቱ በየደረጃው ለሚገኙ የአስተዳደር እርከኖች ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

4. Each executive organs institution shall have head and, as the case may be, deputy head as well as process owners and workers;

5. Executive organs institutions which have related duties may use together a single supportive works center;

6. Executive organ institutions at different levels may be organized or collided at the administration hierarchy.

## 34. Accountability, Power and Duty of Executive Bodies Office's Heads:-

1. Heads of executive organs institutions that are members of executive council shall be accountable to the chief executive and executive council;

2. Each executive institution head;

   a. Assure the implementation of power and duty given to the bureau;

   b. Represent and administer the Bureau;

   c. Manage duties and workers;

   d. Prepare plan and budget, implement the same upon permission and report the execution to Executive Council;

   e. Undertake other duties entitled by the law to the Bureau.

3. The provisions in sub-article (1) and (2) of this article may be implemented by different levels of the administration hierarchy.

## ክፍል ስድስት

### ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**35. አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ስለማደራጀት**

የመስተዳድር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ በማውጣት፣ ማንኛውም አስፈጻሚ አካል እንዲታጠፍ ወይም ከሌላ አስፈጻሚ አካል ጋር እንዲዋሃድ ወይም እንዲከፋፈል ወይም ተጠሪነቱ ወይም ሥልጣንና ተግባሩ እንዲለወጥ ወይም አዲስ አስፈጻሚ አካል እንዲቋቋም በማድረግ የክልሉን መንግሥት አስፈጻሚ አካላት መስሪያ ቤቶችን የማደራጀት ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**36. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1) ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችን መስተዳድር ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፡፡

2) ይህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎችን የመስተዳድር ምክር ቤት አባል የሆኑ የአስፈፃሚ አካላት መስሪያ ቤቶች ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

**37. የተሻሩ ሕጎች**

1) የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 133/2003 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

2) ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**38. መብትና ግዴታዎች ስለማስተላለፍ**

1) የተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍን የሚመለከቱ የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለግብርና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፡፡

## Part Six

### Miscellaneous Provisions

**35. Re-organization of Executive Organs**

Administrative council is hereby empowered, where it finds necessary, to reorganize the executive organs by issuing regulations for the closure, merger or division of an existing executive organs or for change of its accountability or mandates, for the establishment of a new one.

**36. Power to Issue Regulation and Directives**

1. Administrative council may issue regulations that help to implement this proclamation;
2. Executive organ organizations, which are member of Administrative council, may issue directives that help to implement his proclamation, and regulations which may be issued following this regulation to implement the proclamation.

**37.Repeal Laws**

17. The redefinition of powers and duties of the executive organs of southern nations, Nationalities and peoples' government proclamation No 133/2010 is repealed by this this regulation;
18. No proclamation, regulations, directives or practices shall, in so for as they are inconsistent with this proclamation, have force or effect with respect to matters covered by this regulation.

**38.Transfer of Rights and Obligations**

1. The rights and obligations of natural resource and environmental protection relating to the natural resource development sector are hereby transferred to Agriculture and natural resource

2) የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ግብይት ስራዎችን የሚመለከቱ የግብይትና ሕብረት ሥራ ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለግብርና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፡፡

3) የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ዘርፍ የሚመለከቱ የግብርና ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት ቢሮ ተላልፈዋል፡፡

4) ከአነስተኛ የመስኖ ልማት ስራዎች በስተቀር ሌሎች የመስኖ ግንባታና የተቋማት አስተዳደር ስራዎችን የሚመለከቱ የግብርና ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለውሃና መስኖ ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፡፡

5) የግብይት ዘርፍን የሚመለከቱ የግብይትና ሕብረት ሥራ ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፡፡

6) የንግድና የኢንዱስትሪ ዘርፍን የሚመለከቱ የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፡፡

7) የከተማ እና የቤቶች ልማት ዘርፍን የሚመለከቱ የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለከተማ ልማትና ቤቶች ቢሮ ተላልፈዋል፡፡

8) የወጣቶችን ጉዳዮች የሚመለከቱ የሴቶች፣ሕፃናት እና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ተላልፈዋል፡፡

2. The rights and obligations of marketing and cooperative Bureau relating coffee, tea and spice marketing works are hereby transferred to the Agriculture and natural resource development Bureau by this proclamation;

3. The rights and obligations of Agriculture Bureau relating animals and Fish resource development are hereby transferred to fish resource Bureau by this proclamation;

4. The rights and obligations of Agriculture Bureau relating other Irrigation Building and institutions administration works except small irrigation resource development are here by transferred to water and Irrigation Development Bureau by this proclamation;

5. The rights and obligations of marketing and cooperative Bureau relating marketing sector are here by transferred Trade and Industry Development Bureau by this proclamation;

6. The rights and obligations of Trade, Industry and urban Development Bureau relating trade and Industry sector are hereby transferred Trade and Industry Development bureau by this proclamation;

7. The rights and obligations of Trade, Industry and urban Development Bureau relating urban and housing Development are hereby transferred to urban Development and Housing Bureau by this proclamation;

8. The rights and obligations of women, children and youths Affair Bureau relating Youths affairs are here by transferred to youths and sport Bureau by this proclamation;

9) የአካባቢ ጥበቃ ዘርፍን የሚመለከቱ የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለአካባቢ ጥበቃና የደን ባለሥልጣን ተላልፈዋል፡፡

10) የደን ልማትና ጥበቃ ዘርፍን የሚመለከቱ የግብርና ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለአካባቢ ጥበቃና የደን ባለሥልጣን ተላልፈዋል፡፡

**39. አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ _________ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሀዋሣ ______/2008 ዓ.ም**

**ደሴ ዳልኬ**

**የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**

9. The rights and obligations of Natural resources and Environmental Protection Authority relating Environmental Protection sector are hereby transferred to Environmental protection and forest authority by this proclamation;

10. The rights and obligations of Agriculture Bureau relating forest Development and protection sector are hereby transferred to Environmental protection and forest Authority by this proclamation.

**39.Effective Date**

This proclamation shall come to force ---date

Done at Hawassa--------------------2015

Dese Dalke,

Southern Nations, Nationalities and Peoples

Regional Government,

President